ትምህርት ሚኒስቴር
MINISTRY OF EDUCATION

የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት
Educational Assessment And Examinations Service

# የ2014 ትምህርት ዘመን
# የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት
# ማጠናቀቂያ (12ኛ ክፍል) ፈተና አፈጻጸም
# አጭር ሪፖርት

ጥቅምት 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ -ኢትዮጵያ

## Contents

ገጽ

Executive Summary....3

1. መግቢያ ....4

2. መሠረታዊ መረጃዎች ....6

3. የፈተና አስተዳደር ሥራዎች አደረጃጀት....6

4. የሰው ኃይል ምልመላ፣ ምደባና ስምሪት ....7

5. የፈተና ዝግጅት፣ ስርጭትና ክዘና ....8

6. የተፈታኞች ወደ መፈተኛ ማዕከላት ምደባና ትራንስፖርት....9

7. የፈተና አሰጣጥና የጊዜ ሰሌዳ....9

8. የፈተና ኩረጃና ስርቆት....10

ከፈተና ባሻገር ....12

**I. ተግዳሮቶችና የተፈቱበት ስልት**....13

**II. የተገኘው ትምህርትና ትሩፋት** ....15

ሪፖርት የተደረጉ የፈተና ደንብ ጥሰቶችና እርምጃዎች ....18

1. ተንቀሳቃሽ ስልክ ይዞ በመፈተኛ ክፍል/ በመፈተኛ ማዕከል ግቢ ውስጥ መገኘት ወይም መጠቀም......18

2. ጫት እና ሌሎች አደንዛዥ እጾችን እንዲሁም አልኮል/አረቂ ይዞ መገኘት....19

3. የጦር መሣሪያ እና ስለቶችን/ዱላ ይዞ መገኘት....19

4. ፈታኞችን ወይም ሌሎች ተፈታኞችን በግል ወይም በቡድን ሆኖ የማስፈራራት ....19

5. ፈታኞችን አባረው ወይም አስፈራርተው በቡድን መኮረጅ ....20

6. አንፈተንም ብሎ በኃይል በማመጽ ፈተናውን ትቶ ከመፈተኛ ማዕከል በራስ ፈቃድ መሄድ ....21

7. አርፍዶ ወደ መፈተኛ ክፍል ለመግባት መሞከር ....22

8. ከመፈተኛ ማዕከል አጥር ዘሎ መውጣት/መሞከር ወይም ተደብቆ ወጥቶ መጠጥ ጠጥቶ ለመግባት መሞከር....23

9. ወደ መፈተኛ ክፍል ሲገቡ አንፈተሽም ብሎ ከፈታሾች ጋር መጋጨት....23

10. ለሌሎች መፈተን ....24

11. ፌዴራል ፖሊስ ከግቢ ይውጣልን ብሎ ብሎ መረበሽ ....24

12. ተሰብስቦ ከፍተኛ ድምጽ እያሰሙ መጮህ/መጨፈር አልፎ አልፎም ሲጋራ ማጨስ....24

13. የመልስ ወረቀት ሳያስረክቡ ይዞ ለመውጣት መሞከር....24

14. ፈታኞችን እና ፖሊስን በአስጸያፊ ስድብ መሳደብ....24

15. የፈተና ወይም የመልስ ወረቀት ቀድዶ ጥሎ መውጣት/መረበሽ ....25
16. በዩኒቨርሲቲ ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ....25
17. አሉባልታዎችን ማውራት ....25
18. በፈታኞች የተፈጸመ ....26
19. በፖሊስ አባላት የተፈጸሙ ....26
ያጋጠሙ ችግሮች ቀጣይ አቅጣጫዎች ....28
1. የመሻገሪያ ድልድይ መደርመስ ....28
2. የመንገድ ጉዞ ላይ ያጋጠሙ የትራፊክ አደጋዎች ....28
3. የተፈታኞችና የፈተና አስፈጻሚዎች መታመም ....29
4. ወደ መፈተኛ ማዕከል ከገቡ በኃላ የወለዱ ተፈታኞች (ወሊድ) ....30
5. በተፈታኞችና በፖሊስ መካከል ግጭት ....31
6. በተፈታኞች መካከል የቡድን ፀብ ....31
7. የተሳሳተ መረጃ (የገለጻ ችግር) ....31
8. የፈተና ሸራ ላይ መግለጫና የውስጥ የታሸገ ፖስታ መግለጫ መለያየት ....32
9. ከፈተና ጥያቄ ዝግጅት አንጻር ....32
10. ምስጋና ....33
11. ማጠቃለያ ....34

## Executive Summary

የ2014 ትምህርት ዘመን የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ (12ኛ ክፍል) ፈተና የሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ከፍተኛ የአመራር ቁርጠኝነት የታየበት፣ ያልተጠቀምነውን የውስጥ አቅም በአግባቡ የተጠቀምንበት፣ ባለድረሻ አካላት በቅንጅት የሠሩበት ስኬታማ ስራ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። የፈተና ስርቆትን ከዝግጅት እስከ ስርጭትና አሰጣጥ ድረስ በከፍተኛ ደረጃ መቆጣጠር በመቻሉ ሊሰርቁ የሚፈልጉ አካላት ያደረጉት ሙከራ ሁሉ ከሽፎ ፈተናው አልተሰረቀም። ፡ በመፈተኛ ክፍል ውስጥ የሚካሄደውን ኩረጃም ቢሆን በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ተችሏል። በአሰጣጡ ሂደት የተለያየ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች ያጋጠሙ ቢሆንም ከባለድርሻ አካላት ጋር በነበረው ቅንጅት የከፋ ጉዳት ሳያደርሱ መቆጣጠርና ፈተናውን በስኬት ማጠናቀቅ ተችሏል።

በፈተናው ሂደት ውስጥ ከፈተናው ባሻገር በርካታ ለሀገር ግምባታ፣ ለህዝቦች እርስ በእርስ ትስስር፣ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለእርስ በእርስ ትስስር፣ ለባህል ግምባታ… ወዘተ እጅግ ጠቃሚ መልካም ተሞክሮዎች የተወሰዱበትና ትምህርትም የተገኘበት ነው። ከሁሉ በላይ ሁሉም ማለት በሚቻል ደረጃ አብዛኛው ተፈታኝ፣ የተፈታኝ ቤተሰቦችና በሂደቱ የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት በመልካም ጎኑ የተቀበሉትና ያበረታቱት የፈተና ስርዓት ሆኖ ተገኝቷል።

በሂደቱ የተለያዩ የተከለከሉ ተግባራት በመፈጸማቸው በህግ ቁጥጥር ስር የዋሉ ተፈታኞችና ፈታኞች በፌዴራል ፖሊስና በፌዴራል የፍትህ ተቋማት ተገቢው ህጋዊ እርምጃዎች የሚወሰድ ይሆናል። በተፈታኞች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን በቀረበው ማስረጃ መሠረት የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት እያወጣ የሚወስድ ሲሆን በፈታኞችና በፖሊሶች የታየውን ጉድለት ተቋማቱ የሚወስዱ ይሆናል። በቡድን በራሳቸው ፈቃድ አንፈተንም ብለው የወጡ ተፈታኞች ለነሱ ብቻ የሚመቻች ልዩ የፈተና ፕሮግራም በቀጣይ ጊዜ አይኖርም። ነገር ግን በህመም፣ በተፈጥሮ አደጋ፣ በወሊድ፣ በቤተሰብ ውስጥ የቤተሰብ አባልን በሞት በማጣትና በመሰል ችግሮች ያልተፈተኑት ተፈታኞች በቀጣይ በአጭር ጊዜ በሚሰጥ ፈተና የሚፈተኑ ይሆናል። በተለይም በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ በድልድይ መደርመስ ምክንያት ያልተፈተኑ ተፈታኞች እና በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ የፈተና ቡክሌት በማነሱ ምክንያት ዘግይተው የተፈተኑ ተፈታኞች ፍቃደኛ ከሆኑ በቅርቡ የሚሰጠውን ፈተና መፈተን የምችሉ ይሆናል።

1. መግቢያ

ምንም እንኳን ችግሩ ውሎ ያደረ ቢሆንም በ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል የ2013 ዓ.ም ፈተና ሂደትና ውጤት ማሳወቅን ተከትሎ የተከሰተው ውዝግብ የ12ኛ ክፍል ፈተናን ከአጠቃላይ ትምህርት መውጫ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ መመዘኛነት ወጥቶ የፖለቲካ አጀንዳ ማራመጃና የማህበራዊ ሚዲያ የንግድ ማዕከል መሆኑን በግልጽ የተረዳው ሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ይህን ሂደት መስበር እንደሚያስፈልግ ቁርጥ ውሳኔ ወስኗ። ውሳኔውን ወደ ተግባር ለመቀየር የተጀመሩ ሂደቶችን ከመፈተሽ ጀምሮ ሁሉንም አማራጮች ተንትኖ የ2014 ዓ.ም ፈተናን በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በዩኒቨርሲቲ መምህራን መፈተን እንዳለበት ወስኖ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲገባ ሂደቱ ብዙ አካላትን የሚያሳትፍ፣ ብዙ ሎጅስትክስ እንደሚያስፍልግ በግልጽ የሳየ ነበር። ይህንንም በሙሉ ቁርጠኝነት በመያዝ ከመንግስት ከፍተኛ አመራሮችና ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር የተደረጉ ውይይቶችን በመከተል የውሳኔውን ትክክለኛነት ብቻ ማረጋገጥ ሳይሆን የሚጠይቀውን ሀብት ካለው ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልክ እንዲመደብ ተደረጓል።

ይህ ውሳኔ አገሪቱ የውጭ ድጋፍ በተነፈገችበት እና የውስጥ ሀብቷን ህልውናዋን ለማረጋገጥ በከፍተኛ ደረጃ ባዋለችበት ሁኔታ ለመወሰን ያስፈለገበት ምክንያት ትምህርት የሁለመናችን መሠረት እና የለውጥ መዳረሻ መጀመሪያ መሆኑን በመረዳት ነው። ዝግጅታችን የፀጥታ፣ የደህንነት፣ የክልል/የከተማ አስተዳደር መንግስታት፣ የትምህርት አመራርና ሁሉንም ዩኒቨርሲቲዎች ተከታታይነት ያለው ግንኙነትና ውይይቶች አልፏል።

በፈተናው መጀመሪያ ወቅት በተሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ እንደተገለጸው ፈተናውን ልዩ የሚያደርገው ከተለመደው በተለየ መልኩ ለመፈተን መዘጋጀታችን ብቻ ሳይሆን በአገራችን ታሪክ ተፈትኖ የማያውቅ ግዙፍ ቁጥር ማለትም 976፣018 ተመዝጋቢዎችን ነው ለመፈተን የተዘጋጀነው፡ ፡ ይህ ቁጥር በአፍሪካ ውስጥ ብዙ ከተሞችን እንዲሁም የደሴት አገራትን ካላቸው ጠቅላላ ህዝብ በላይ ቁጥር መሆኑን ማስተዋል እጅግ ተገቢ ነው።

በዚህም ምክንያት ዩኒቨርሲቲዎቻችን ያላቸውን አቅም አሟጠው እንዲሰጡ ተደርጎ ተፈታኞችን በሁለት ዙር መፈተን የሚቻልበት ዝግጅት ተደርጓል።

ይህ የአፈታተን ስርዓት የፈተና ስርቆትንና ኩረጃን በከፍተኛ ደረጃ ለመቆጣጠርና ለመቀነስ፣ የፈተና ደንብ ጥሰቶችን በብቃት ለመከላከልና ተመጣጣኝ እርምጃዎችን ለመወሰድ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ

ለመፍጠር፣ የፈተና ሂደቱና ውጤቱም ተገቢ ካልሆነ ወገንተኝነት ለማላቀቅ፣ ፈተናንና የፈተና ውጤትን ካልተገባ የፖለቲካ መጠቀሚያነት ለማላቀቅ… ወዘተ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ፈተና መስጠት አሁን ካሉት የተሻለ አመራጭ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ይህም ተፈታኞቹ በተወሰነ ደረጃ ስለዩኒቨርሲቲ አካባቢ መረጃ እንዲኖራቸው፣ ዩኒቨርሲቲዎቹም ስለተፈታኞቹ የተሻለ መረጃ እንዲኖራቸው፣ የፈተና አስተዳደር ሥራው ለቁጥጥር ምቹ እንዲሆን ከማድረግ አንጻር የጎላ ጥቅም አስገኝቷል፡፡ በተጨማሪም ወደፊት ዩኒቨርሲቲዎች ራሳቸውን ችለው ተማሪዎቻቸውን የመግቢያ ፈተና ፈትነው ለመቀበል ልምድ እንዲያካብቱ፣ ከንብረት ውድመት አልፎ እስከህይወት መስዋዕትነት እያስከፈለ ያለውን የፈተና ስርቆትንና ኩረጃን ለመቀነስ፣ የተበታተነ የፈተና አስተዳደርን ሰብሰብ ለማድረግ፣ ለፈተናው በቂ ዝግጅት ያደረጉትን እና ጎበዝ ተማሪዎችንና ቤተሰቦቻቸውን ለማበረታታት፣ እንዲሁም ከተዛባ የማህበራዊ ሚዲያ መረጃዎች እና ከሚፈጥሩት አሉታዊ ስነ ልቦና ጫና ለመከላከል በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ፈተናውን መስጠቱ ጠቅሟል፡፡

# ክፍል አንድ

## 2. መሠረታዊ መረጃዎች

የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ (12ኛ ክፍል) ፈተና ላይ የነበሩ መሠረታዊ መረጃዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.1. የተፈታኞች መረጃ

| ዘርፍ (Stream) | የተፈታኞ (ዕቅድ) | የተፈተኑ (አፈጻጸም) | ያልተፈተኑ | |
|---|---|---|---|---|
| | ድምር | ድምር | ብዛት | በ% |
| ማህበራዊ ሳይንስ | 595,700 | 586,541 (98.5%) | 9,159 | 1.54 |
| የተፈጥሮ ሳይንስ | 352,622 | 350,505 (99.4%) | 2,117 | 0.60 |
| ጠቅላላ ድምር | 948,322 | 937,046 (98.8%) | 11,276 | 1.19 |

### 2.2. የፈተና አስፈጻሚዎች መረጃ

| ተቁ | ኃላፊነት | የተመደቡ | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | ማዕከል ኃላፊ | 133 | |
| 2 | የጉድኝት ማዕከል አስተባባሪ | 133 | |
| 3 | ጣቢያ ኃላፊ | 2,567 | |
| 4 | ሱፐርቫይዘር | 3,538 | |
| 5 | ፈታኝ | 18,490 | |
| 6 | አንባቢ | 567 | |
| 7 | ፖሊስ | 7,128 | ፈተና አጃቢ=708፤ ከክልል ሴት ፈታሽ 692) |
| 8 | ቆጣሪ | 417 | |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **32,973** | |

## 3. የፈተና አስተዳደር ሥራዎች አደረጃጀት

በበሀገር አቀፍ ደረጃ በትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር የሚመራ ሀገራዊ ግብረ ሓይል የነበረ ሲሆን ቴክኒካዊ ሥራዎች ደግሞ በትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ሲመሩ ቆይተዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በክልል/በከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊዎች የሚመራ ግብረ ኃይል ሁሉንም ክልላዊ ሥራዎች ሲመራ የቆየ ሲሆን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የነበረው ግብረይል ደግሞ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚሰሩ የአስተዳደር ሥራዎችን ሲመራ ነበር፡፡

በሁሉም መዋቅር ደረጃ የተቋማቱ የበላይ ኃላፊዎች የሚመሩት ሆኖ ቋሚ አባላቱም በየደረጃው ያሉ የጸጥታ አካላት፣ የመንገድ ደህንነት፣ ትራንፖርትና ሎጅስቲክስን የሚመሩ አካላት፣ የአካባቢ መስተዳድር አካላት በዋናነት አባላት ሆነው ሰርተዋል፡፡በፌዴራል ደረጃ የነበረው የፈተና ሥራውን ለሚመሩና ለሚያስተባብሩ አካላት የተሰጠው አመራር ሥራው የተሳለጠ እንዲሆንና ወጥ የሆነ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር አድርጓል፡፡ በተለይም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ለሁሉም ፈታኞችና የፈተና አስፈጻሚዎች መልዕክት እንዲያስተላልፉ መደረጉ በፈታኞችና በፈተና አስፈጻሚዎች ዘንድ ትልቅ መነቃቃትንና የኃላፊነት ስሜትን ፈጥሯል፡፡

## 4. የሰው ኃይል ምልመላ፣ ምደባና ስምሪት

### 4.1. የሰው ኃይል ምልመላ

ፈተናውን ከትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት በኃላፊነት ተቀብለው የሚያስተዳደሩ 133 የማዕከል ኃላፊዎች በትምህርት ሚኒስቴር፣ ከትምህርት ምዛናና ፈተናዎች አገልግልትና ከትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን ተቋማት በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የተሻለ የሥራ ተነሳሽነት፣ ዝግጁነትና ብቃት ያለቸው ተመልምለዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የፈተናውን ቴክኒካል የማስተዳደር ሥራን የሚመሩና የሚያስተባብሩ የጉድኝት ማዕከል ኃላፊዎች (133)፣ የጣቢያ ኃላፊዎች (2,567)ና ሱፐርቫይዘሮች (3,538) ከክልልና የከተማ አስተዳደር የትምህርት ቢሮዎችና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቀድሞ በነበራቸው አፈጻጸም፣ አሁን ባላቸው የሥራ ተነሳሽነትና ዝግጁነት እንዲሁም ዝርዝር የምልመላ መስፈርት መሠረት ተመልምለዋል፡፡

በሌላው በኩል ፈታኞችና የአይን ስውር ተፈታኞች አንባቢዎች ከዩኒቨርሲቲ መምህራን በፈቃደኝነት፣ በሥራ ተነሳሽነት፤ ዝግጁነትና በሌሎች ዝርዝር የምልመላ መስፈርቶች መሠረት ተመልምለዋል፡፡ በተመሳሳይ የመልስ ወረቀት አደራጆችም ከዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ አባላት ተመልምለው የፈተና ሥራውን ሠርተዋል፡፡

### 4.2. የሰው ኃይል ምደባና ስምሪት

መሠረታዊ መርሆ፡- ማንኛውም ፈታኝና የፈተና አስፈጻሚ የሚሰራበት ተቋም ካለበት ክልል፣ የትውልድ ቦታ (ብሔሩ) ከሚገኝበት ክልል እና ተመሳሳይ ብሔር ያላቸው ተፈታኞች ከተመደቡበት መፈተኛ ማዕከል ውጪ ተመድበዋል፡፡ በዚሁም መሠረት ፈታኞች የሆኑ የዩኒቨርሲቲ መምህራን የሚሰሩበት ዩኒቨርሲቲ ካለበት ክልል፣ ከተወለዱበት ክልል እና የተወለዱበት አካባቢ ተፈታኞች ካሉበት መፈተኛ ማዕከል ውጪ ተመድበው ሠርተዋል፡፡ የምደባ ሂደቱም ለዚሁ አግልግሎት በተቋማችን በለማ ሶፍትዌር ተሠርቷል፡፡ የምደባ መልዕክቱም በ9010 በቀጥታ ስልካቸው

እንዲደርስ ተደርጓል። በተመሳሳይ መልኩ ፈተናውን አጅበው የሄዱ የፌዴራል ፖሊስ አባላት ከተለያየ ምደብ የመጡትን በመበወዝ ምደባ ተሰጥቷቸዋል።

የሰው ኃይል ስምሪቱም በየፈተና ማዕከሉ የፈተናውን ሥራ ለሚመሩ የማዕከል ኃላፊዎችና የጉድኝት ማዕከል አስተባባሪዎች በፌዴራል ደረጃ በቂ ገለጻ በስልጠና መልክ የተሰጣቸው ሲሆን በተዋረድ ለሁሉም በፈተና ማዕከላት ገለጻ እንዲያገኙ ተደርጓል።በተጨማሪም ሁሉም ፈታኝና የፈተና አስፈጻሚ ማንኛውንም ላሉበት ሁኔታ የሚመች የአየርና የየብስ ትራንስፖርት እንዲጠቀሙ ተፈቅዷል።

## 5. የፈተና ዝግጅት፣ ስርጭትና ክዘና

### 5.1. የፈተና ዝግጅት

የፈተናው ዝግጅት በተቋሙ የተሰራ ሲሆን ከስርጭት በፊት የፈተና ስርቆት እንዳይኖር ለመከላከል የ24 ሰዓት አካላዊ ጥበቃ ከመደረጉም ባሻገር የሳይበር ጥቃት እንዳይፈጸም ከኢንተርኔት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላቸው ኮምፒውተሮችን ተጠቅመናል። በተጨማሪም ለፈተና ዝግጅት የሚያገለግሉ ሶፍትዌሮች ሥራ ከመጀመሩ ቀድሞ የደህንነት ፍተሻ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ተደርጎላቸዋል። ተያይዞም የፈተና ማዘጋጃ የ24 ሰዓት በደህንነት ካሜራ ክትትልና ቁጥጥር ሥራም ታግዞ ተሠርቷል።

### 5.2. የህትመት ሥራ

ፈተና ሊሰረቅ ከሚችልባቸው ቦታዎች አንዱ የፈተና ህትመት ቦታ በመሆኑ የህትመት ቦታው ህትመት ከመጀመሩ በፊት ማተሚያ ክፍሎቹና ግቢው ሙሉ አካላዊ የደህንነት ፍተሻ ተደርጓል። በተያያዘም ለህትመት አገልግሎት የሚውሉ ማሽኖችና ኮምፒውተሮች ከኢንቴርኔት ጋር ግንኙነት እንዳይኖራቸው የተደረገ ሲሆን የሚጠቀሙባቸው ሶፍትዌሮችም የደህንንት ፍተሻ ተደርጎላቸዋል።

ከዚህ ባሻገር በህትምት ክፍል ሥራ የሚሰማሩ ሠራተኞች ምልመላ በጥንቃቄ የተካሄደ ሲሆን የ24 ሰዓት አካላዊ ጥበቃ በፌዴራል ፖሊስ በከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጓል። በተጨማሪም የ24 ሰዓት የደህንነት ካሜራ ክትትል ተደርጓል። ከዚህም ባሻገር ለህትመት ሥራዉ በቂ የሰው ኃይል በመመደብ እና 24 ሰዓት በመጠቀም ሁሉም ፈተና ባጠረ ጊዜ ውስጥ ፖስታ ውስጥ ገብቶ እንዲታሸግ ተደርጓል።

### 5.3. የፈተና ስርጭትና ክዘና

እስካሁን ባለው ሪፖርትና ግንዛቤ በጣም ትልቁ የፈተና ስርቆት የሚካሄደው በስርጭት ጉዞ ወቅትና በክዘና ማዕከላት ነው፡፡ ይህንን ስጋት ለመቅረፍ የፈተና ማዕከላቱ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ መሆኑ በከፍተኛ ደረጃ ጠቅሟል፡፡ በዚሁ መሠረት አብዛኛውን የስርጭት ጉዞ በአየር መንገድ ማድረግ የተቻለ ሲሆን የደህንነት ስጋት ያለባቸው አካባቢዎች ላይ በሄሌኮፕተር ጭምር በመታገዝ ተሠርቷል፡፡

በአጭርም ይሁን በረጅም የየብስ ጉዞ ባለባቸው ቦታዎች ሁሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ የተደረገበት በፌዴራል ፖሊስ እጀባ ተደረጓል፡፡ በክዘና ቦታዎችም ክፍሎቹ የደህንነት ፍተሻ የተደረገላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ አጅቦ መውሰድና የ24 ሰዓት ጥበቃ የማድረግ ሥራ የሚሰሩ የፌዴራል ፖሊስ አባላትን ከፍተሻና ከሌሎች የጸጥታ ሥራዎች ለይቶ በቋሚነት ምደባ በማድረግ ተሠርቷል፡፡ በተጨማሪም ፈተናውን በየመፈተኛ ማዕከሉ አንድ ሰው ብቻ በኃላፊነት እንዲረከብ ተደርጓል፡፡

## 6. የተፈታኞች ወደ መፈተኛ ማዕከላት ምደባና ትራንስፖርት

መሠረታዊ መርሆ፡- ሁሉም ተፈታኝ ባለበት ክልል ውስጥ ባሉ መፈተኛ ማዕከላት (ዩኒቨርሲቲዎች/ከምፓሶች) ውስጥ መመደብ ቀዳሚ ትኩረት ነበር፡፡ ይህም ለትራንስፖርት የሚውሉ መኪናዎችን ከፍተኛ እጥረትና የሚያስፈልገውን ከፍተኛ ወጪ ለመቆጠብ እንዲያግዝ የታሰበ ከመሆኑም ባሻገር የተፈታኞችን የጉዞ ላይ ደህንነት ከማረጋገጥ አንጻርም ለክልሎች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር አግዟል፡፡

በዚሁ መሠረት የተፈታኞቹ ቁጥር በክልሎቹ ካሉ የመፈተኛ ማዕከላት የመያዝ አቅም ጋር ባለመመጣጠኑ ከኦሮሚያ ወደ ሲዳማ፣ ቤ/ጉ፣ ሶማሌ፣ ደብብህክ ክልሎች ላይ እና ከሲዳማ ወደ ደብብህክ ላይ የተወሰኑ ተማሪዎች ምደባ የተደረጉ ሲሆን ርቀት ከመቀነስ አንጻር ከሶማሌ ወደ ሲዳማ እና ከጋምቤላ ወደ ደምኢህ የተወሰኑ ተፈታኞች በክልል ትምህርት ቢሮዎች ይሁንታና ኃላፊነት ተመድበው ተፈትነዋል፡፡ በክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ አመራርና ሠራተኞች ተፈታኞችን ከወረዳና ከዞን ማዕከላት ወደ መፈተኛ ማዕከላት የማጓጓዝና የማስፈተሽ እንዲሁም በተዘጋጀው የፈተና ማስፈጸሚያ ማንዋል ላይ ገለጻ የመስጠት ሥራ ተሠርቷል፡፡

## 7. የፈተና አሰጣጥና የጊዜ ሰሌዳ

### 7.1. የፈተና አሰጣጥ

ከሁሉ በላይ የዩኒቨርሲቲዎች የበላይ አመራሮች የፈተናውን ሥራ በባለቤትነት ይዘው እንዲመሩት ማድረግ መቻሉ እና በቅርበትም ክትትልና ድጋፍ መደረጉ የፈተና አሰጣጥ ሂደቱ የገጠሙትን መሰናክሎች ማለፍ እንዲችልና አሉታዊ ተጽኖዎችን የመቋቋም አቅሙ እንዲጎለብት አድርጎታል፡፡ የፈተና አሰጣጥ ሂደቱ የተሳለጠ እንዲሆን የፈተና አሰጣጡ ላይ በቂ ቅንጅት እንዲኖር የማዕከል

ኃላፊዎቹ ከ15 ቀን በፊት በየፈተና ማዕከላት በመገኘት ከተቋማቱና ከመሠረተ ልማቶቹ ጋር በቂ ትውውቅ ማድረጋቸው የሰው ኃይልን ስምሪቱንና አጠቃላይ ሎጂስትኩን በተሳለጠ መልኩ እንዲመሩ አግዟል፡፡

### 7.2. የፈተና የጊዜ ሰሌዳ

የፈተና የጊዜ ሰሌዳው ቀድሞ በደንብ የታሰበበት፣ በማህበራዊና በተፈጥሮ ሳይንስ ተፈታኞች መካከል ያለው ቅንጅት የተፈጠረበት፣ ጠዋትና ከሰዓት ፈተና መጀመሪያ ሰዓቶች የተቃኙበት መንገድ ነባራዊውን ሁኔታ ያገናዘቡ በመሆናቸው ውጤታማ የፈተና አሰጣት ሂደት እንዲኖር አግዘዋል፡፡

## 8. የፈተና ኩረጃና ስርቆት

### 8.1. የፈተና ስርቆት

በባለፉት አመታት በተለይም ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ የፈተና ስርዓቱን ከተፈታተኑ ጉዳዮች ዋንኛው የፈተና ስርቆት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ነገር ግን በ2014 ዓ.ም የፈተና አፈጻጸም አስካሁን ባለን ሁሉ አቀፍ ተቋማዊ ክትትል በተገኘው መረጃ መሠረት የፈተና ስርቆት አልተፈጸመም፡፡ ፈተና አልተሠረቀም፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የዕለቱ ፈተና ከተጀመረ በኃላ በተለያዩ የማጭበርበሪያ መንገዶች ተንቀሳቃሽ ስልክን ወደመፈተኛ ክፍል ይዘው በገቡ ተፈታኞች የአንዱን ኮድ የተወሰኑ የፈተና ገጾች በቴሌግራም ሲላላኩ ታይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ላኪውም ሆነ ተቀባዩ ምንም ዓይነት አሉታዊ ተጽዕኖ በፈተና ስርዓቱ ላይ መፍጠር አልቻሉም፡፡ ምክንያቱም ተፈታኞቹ ጥብቅ ቁጥጥር በሚደረግበት ፈተና ክፍል ውስጥ ባሉበት ወቅት የተደረገ ከመሆኑም ባሻገር ስልክ ይዘው ያልገቡ በመሆኑ እና በፈተና ወቅት ቴልግራም ዝግ የነበረ በመሆኑ ከሽፏል፡፡

የፈተና ስርቆት ጥረቶቹ ፈተናውን ሰርቆ ከመስራት በዘለለ የፈተና ስርዓቱን ለማደናቀፍ የተደረገ ያልተሳካ ጥረት ሲሆን ብሔራዊ መረጃ መረብ ደህንንት አስተዳደር የለያቸውን እና በፌዴራል ፖሊስ ክትትል ስር 33 ግልሰቦች ይገኛሉ፡፡

### 8.2. የፈተና ኩረጃ

ኩረጃን ለመከላከል የፈተና ኮዶችን መጨመር፣ የተፈታኞችን ቁጥር በአንድ መፈተኛ ክፍል 36 እና ከዚህ በታች እንዲሆኑ የማድረግ፣ የተፈታኞች የክፍል ውስጥ አቀማመጥን ለኩረጃ እንዳይመች የማድረግ፣ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ፣ ወዘተ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡

ሆኖም በጉልበትና በዐመጻ በግልም ይሁን በቡድን የኮረጁትን የመለየት ሥራ የተሰራ ሲሆን በሁሉም ላይ ከአንድ ፈተና እስከ ሙሉ በሙሉ እስከመሠረዝ የሚደርስ እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

# ከፈተና ባሻገር

ትምህርት ሚኒስቴር እንደ አገር ከተቋቋመበት ከ1923 ዓ.ም ጀምሮ የአገራችንን የፖለቲካ ለውጥና የማህበራዊ እድገት ተከትሎ ብዙ ጉዳዮችን አስተናግዷል። በአገራችን የፖለቲካ ለውጦች እንዲከሰቱ ምክንያት ሆኗል ወይም በለውጦችም ምክንያት በብዙ ተለውጧል። በቅርብ አመታት ትምህርት ለፖለቲካ ትግል መሳሪያ ለመጠቀም በተደረገ ባልተገባ እንቅስቃሴ በትምህርት ተቋማት ደህንነትና በፈተና አስተዳደር ላይ ብዙ ጉዳት ደርሷል። አገራዊ ለውጡ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ያጋጠመን ፈተና በዘላቂነት ለመፍታት የተለያዩ እርምጃዎች ሲወሰዱ የቆዩ ሲሆን የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደህንነት ለማስጠበቅ ሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎችን በፌዴራል ፖሊስ ጥበቃ ስር እንዲሆኑ ተወስኖ ለዚሁ አደረጃጀት ተፍጥሮ ስራ ጀምሯል። በዚህም ከ2013 ጀምሮ በዩኒቨርሲቲዎች እንደዚህ ነው የሚባል የደህንነት ስጋትና የተቋማት የመደበኛ ተግባር የሚያስተጓጉል ወይም እንዲቆራረጥ የሚያደርጉ ክስተቶች አላጋጠሙንም።

የፈተና አስተዳደር ስርዓታችን በተለይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ /የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተናዎችን በሂደት እያጋጠሙ የመጣው ችግር ቀድሞውኑ ስርዓቱ ከነዚሁ ተጋላጭነት ጋር ተደምሮ ፈተና አዘጋጅቶ ሰጥቶ ማጠናቀቅ አስቸጋሪ ፈተና ውስጥ ወድቆ ቆይቷል። በባለፉት ሶስት አመታት የፈተና ዝግጅቱን አሰጣጡንና እርማቱን በቴክኖሎጂ ሙሉ በሙሉ ለመስራት እንቅስቃሴዎች የነበሩ ቢሆንም ለዚሁ የሚያስፈልገውን በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ታብሌት ኮምፒዮተር በወቅቱ ማግኘት ባለመቻሉ የ2013 ፈተና ዘግይቶ በ2014 ጥቅምትና ጥር እንዲሰጥ ተደርጓል። በ2013 ፈተና አሰጣጥ ወቅት ያጋጠሙን ችግሮች የፈተና ውጤት መገለጽን ተከትሎ የተፈጠሩ ውዥንብሮች፣ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት ለመጀመሪያ ጊዜ በፖሊሲው መሰረት ሃምሳና ከዚያ በላይ እንዲሆን መወሰኑ ወዘተ ለተጨማሪ የፖለቲካ ነጥብ ማሰባሰቢያ ስራ ላይ ውሎ ህመሙን በመቻል የቆየውን ስርዓት ወደ ተሟላ ቀውስ ያደረሰው መስሎ ነበር። እንግዲህ ይህ በእንዲህ እንዳለ ነው የ2014 ፈተና እንዴት መሰጠት እንዳለበትና በምን መልኩ ጥያቄ ውስጥ የገባውን ስርዓትና ያለውን ስብራት እናክም የሚለው ውይይት የተጀመረው። ከክልሎች ትምህርት ቢሮዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በተደረጉ በርካታ ተደጋጋሚ ውይይቶች በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ የሚሰሩ ሌሎች ውጤታማ ስራዎች ሳይቀሩ ቅቡልነታቸውን ያጡት የትምህርት ማህበረሰቡና መላው ህዝብ በሃሰተኛ የትምህርት ማስረጃ እና በፈተና አስተደደር ላይ ባለን ሰፊ ክፍተት በተፈጠረበት እምነት ማጣት መሆኑ ግልጽ ሆኖ ወጥቷል።

ስለሆነም በሁለቱ ላይ ፈጣን እርምጃ መውሰድ የቅድሚያ ቅድሚያ ማድረግ እንደሚገባና ለዚህም ተጨባጭ የአመራርና የአሰራር ለውጥ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ነበር የተወሰነው፡፡ ፈተናውን የት እንስጥ፤ ተማሪዎችን እንዴት እናጓጉዝ እና እነ ማንን በፈተና አስፈፃሚነት እንጠቀም የሚለው ላይ መስማማት የመጀመሪያው ፈተና ነበር፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ዘጠኝ መቶ ሺህ ተማሪዎችን እንዴት አድርገን በአንድ ወቅት ፈተና እንስጥ የሚለውን መመለስ በተመሳሳይ በርካታ አማራጮችን ማየት የሚጠይቅ ውስብስብ ጉዳይ ነበር፡፡ በመጨረሻም ፈተናውን በሁለት ዙር (የማህበራዊ ሳይንስ እና የተፈጥሮ ሳይንስ) በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን ወደሚቀርባቸው ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመውሰድ እዛው አድረውና ተመግበው ፈተናውን እንዲወስዱ ማድረግ ፣ ተማሪዎች ወደ ግቢዎች ሲመጡ በትምህርት ተቋማት የተከለከሉ ቁሶች እንዳይዙ ማድረግ እንደተጠበቀ ሆኖ ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች መከልከል፣ ፈተና አስፈፃሚዎችን ከተወለዱበትና ከሚሰሩበት አካባቢ ውጭ አሰባጥሮ መመደብ፣ የፈተናውን ደህንነት ሙሉ በሙሉ በፌደራል ፖሊስ ኃላፊነት እንዲመራ ማድረግ፣ የፀጥታ ችግር ወዳለባቸው አካባቢዎች የፈተና ወረቀትን በከፍተኛ ጥንቃቄና ደህንነቱ ተጠብቆ መውሰድ፤ በተናጠል የየራሳቸውን ፈተና የሚደቅኑ ነበሩ፡፡ በዚህ አጭር መግለጫ የነበሩ አንኳር ተግዳሮቶች እና የታለፈበት መንገድ እንደዚሁም ከፈተናው ባሻገር የተገኙ ትሩፋቶች ቀርበዋል፡፡ ከሁሉ በላይ የተማርነው እንደሀገር ተቀናጅተን ከሰራን ትላልቅ ጉዳዮች መከወን እንደምንችል ያየንበት ስለሆነ ሰንዶ ማስቀመጥ ተገቢ ነው፡፡ ስለዚህም ት/ሚኒስቴር ይህንን ለመጀመሪያ ጊዜ የተጀመረውን የፈተና አሰጣጥ ሂደት በዝርዝር ሪፖርት ሰንዶ አዘጋጅቷል፡፡ ባጭሩ ኢትዮጵያ የአንዳንድ አፍሪካ አገራት ሙሉ ህዝብ በጥቂት ቀናት አንጉዛ፣ በተቋማት መግባ፣ አሳድራ ፈተና መስጠት የሚያስችል አቅም ባለቤት መሆኗን በሂደቱ አረጋግጠናል፡፡

## I. ተግዳሮቶችና የተፈቱበት ስልት

### *ተግዳሮት አንድ ፡- የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ማስተናገድ አቅም እና የማህበራዊ ሳይንስ ተፈታኞች ቁጥር መለያየት*

ተጠሪነታቸው ለትምህርት ሚኒስቴር በሆኑ 43 ዩኒቨርሲቲዎች፣ በፖሊስ ዩኒቨርሲቲ እና በፌደራል ቴክኒክና ሙያ ኢንስቲቲዩት የነበረው የቅበላ /የማስተናገድ/ አቅም በማህበራዊ ሳይንስ መስክ ፈተና ይወስዳሉ ተብሎ ከሚጠበቁ ተፈታኞች ቁጥር በብዙ አስር ሺዎች ያንስ ነበር፡፡ በተጨማሪም ለልዩነቱ ፍራሽ ገዝቶ ዶርሞችን አጣቦ ተማሪ ማስተኛት ቢቻልም ተቋማት የመማሪያ ክፍሎችን እና አዳራሾችን ለፈተና አዳራሽ በማዋል ብቻ የተመደበላቸውን ተማሪ በአንድ ጊዜ መፈተን አይችሉም፡፡ ከሁሉ የባሰው በየእለቱ ሶሶት ጊዜ ምግብ አዘጋጅቶ በነበረው መሰረተ ልማት እና ቁሳቁስ መመገብ ፈተናውን በጊዜው መጀመር ላይ ሌላ የራስ ምታት ነበር፡፡ ከሚገጥሙን

ተግዳሮቶች ሁሉ ለዚህ ውስብስብ ጉዳይ መልስ መስጠት አዳጋች ነበር። በዚህ ጉዳይ ላይ ካለው ተግዳሮት አልፈን ፈተናውን መስጠት እንችላለን የሚለው ስምምነት ላይ መድረስ ትልቅ ድል ነበር። ለዚሁ ሲባል እያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ አለኝ የሚለውን የማስተናገድ አቅም (ለማሳደር ፣ ለመመገብ ፣ ለመፈተን) በዝርዝር እንዲፈትሽና ወደ ስራ ያልገቡ አቅሞችን (ዎርክሾፖች፣ ምርምር ፖርኮችን፣ መመገቢያ አዳራሾችን... ወዘተ) በአጭር ጊዜ አጠናቆ ስራ ማስጀመር፣ መለጠጥ የሚችሉ አቅሞችን መፈተሽ በዚህም የቴሌቪዥን አዳራሾችን እንደ ማደሪያ፣ የመማሪያ ክፍል ኮሪደሮች እንደ መፈተኛ መጠቀም ወዘተ በጥልቀት ማየት የሚጠይቅ ነበር። ለጎደሉን ጉዳዮች አቅሞችን መዋስና ጊዜያዊ መፍትሄዎች በስራ ላይ በማዋል ልዩነቱን ማጥበብ ስለሚገባ በአንዳንድ ቦታዎች ከእድሮች ድንኳን በመከራየት፣ ሳህን በመዋስ የተመደበውን ተማሪ ቁጥር ለማስተናገድ ሌላ ተጨማሪ መፍትሄ ተቀምጦለታል። በመጨረሻም የዚህን ተግዳሮት ጫና ለማስታገስ የመመገቢያ እና የፈተና ማስጀመሪያ ሰዓት ላይ ማስተካከያ ማድረግ ጭምር የውሳኔው አካል እንዲሆን ተደርጓል።

***ተግዳሮት ሁለት ፦ ተማሪዎችን ፣ ፈተና አስፈፃሚዎችንና የፀጥታ ኃይል ማጓጓዝ***

የ2014 ፈተና በዩኒቨርሲቲ ግቢዎችና ካምፖሶች ለመስጠት ከ30 ሺህ በላይ ፈታኞች፣ ሱፐርቫይዘሮች፣ ጣቢያ ኃላፊዎች፣ አስተባባሪዎች እንደዚሁም 937 ሺህ በላይ ተፈታኞች ማጓጓዝ ይጠይቅ ነበር። ፈተናው እንዲሰጥ የታቀደበት ወቅት መስከረም መጨረሻ ትላልቅ አገራዊ በአላት የሚከበሩበት ሲሆን በተጨማሪም የአገር መከላከያ ሰራዊታችን የአገር ሉዓላዊነትና የአገር አንድነት ለማስከበር ሰራዊት ማንቀሳቀስ ያለበት ወቅት ጋር ተደምሮ ጫናውን ግዙፍ ያደርገዋል። ይህ ብቻ ሳይሆን ወደ ተወሰኑ አካባቢዎች መደበኛ ትራንስፖርት በተለመደው አግባብ ማሰማራት ከባድ ነበር። ጤነኛ አዕምሮ ያለው ሰው ይህንን ሁሉ ተግዳሮት መኖሩን እያወቀ እንዴት ወሰነ ብሎ የሚያደንቅ የሚጠይቅና የሚወቅስ አይጠፋም። ይህን የሚያክል ተግዳሮት ተጋፍጦ በጣም ውስን ጉድለቶች አስተናግዶ መጨረስ አስደማሚ መሆኑ አይቀርም። የኢትዮጵያን ትልቅነት ገና ባያክልም፤ በየትኛውም መመዘኛና መስፈርት ይህን የሚያክል ተግዳሮት አውቆ የሚጋፈጥ ትልቅ ስራንና ውሳኔ የሚገኘው ኢትዮጵያ ብቻ ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስደፍር ነው።

***ተግዳሮት ሶስት፦ በቂና ትክክለኛ ፈተና ወረቀት ለሁለቱም ዙር መሰራጨቱን ማረጋገጥ***

በአገራችን ታሪክ የተፈጥሮ ሳይንስና የማህበራዊ ሳይንስ ፈተናዎች ተለያይተው ተዘጋጅተው፣ ታትመውና ተሰጥተው አያውቅም፣፣ ይህ ብቻ ሳይሆን በዚህ ቁጥር ልክ ተፈታኝ ኖሮ ስለማያውቅ በ10ሺዎች ለሚቆጠሩ የፈተና ክፍሎች እና ሰባት ፈተናዎች ተጠንቅቆ በኮረጆ መደልደልና ማሰራጨት ቀደም ተከተሉን ጠብቆ መክዘንና በፈተናው እለት ማሰራጨት የተፈታኙ ቁጥር በዚህ

ልክ ባልበዛባቸው ጊዜያት ጭምር ብዙ ጉድለት ያለበት ነበር፡፡ በዚህኛው ላይ የሚያጋጥመን ክፍተት የሴራ ትንተና በገነነበት በዚህ ወቅት ሌሎች ልፋቶችን ሁሉ የሚያኮስስ ሊሆን ስለሚችል እጅግ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልግ ነበር፡፡ በአንድ ፈተና ማዕከል ሁለት የትምህርት ዓይነት ላይ አጋጥሞን መፍትሄ ከተሰጠው ችግር ባሻገር እንዲህ ነው የሚባል ሳያጋጥም መታለፉ የሚያስደንቅ ነበር፡፡

**ተግዳሮት አራት**፡ ቁጥሩ ጥቂት የማይባል አመራር ቀድሞ በተያዘ መርሃግብር የማይኖር መሆኑ እንደ አገርም ይሁን በሴክተሩ ሁሌም የሚነሳ ግን በቂ መልስ ያላገኘው አንድ ጉዳይ ተቋም ግንባታ ነው፡፡ ተቋማት ተገንብተው በሥርዓት ከተመሩ የግለሰቦች ሚና የመሪዎችን ጨምሮ ሁሉንም የሚወስን ብቸኛ ጉዳይ መሆኑን ያስቀራል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቀድሞ በወጣ ፕሮግራም ዘጠኝ ፕሬዚደንቶችና አስራ ስድስት ምክትል ፕረዚደንቶች ከፈተናው አንድ ሳምንት ቀደም ብለው ጀምረው እስከ ፈተናው ማጠናቀቂያ እለት ለአመራር አቅም ግንባታ ሥልጠና ወደ አሜሪካ የሚሄዱ መሆኑ ሌላ ክፍተት ፈጥሮ ችግር ላይ እንዳይጥለን ማድረግ ያስፈልግ ነበር፡፡ በተጨማሪም የተወሰኑ አመራሮች የማህበራዊ ሳይንስ ሲካሄድ ለአራት ቀናት በተመሳሳይ ሥልጠና ምክንያት አይኖሩም፡፡ በሁለቱም ላይ ጨክኖ መወሰን ይፈልግ ነበር፤ ፕሮግራሞች መሰረዝ ወይም አመራሩን ለሥልጠና ልኮ ባለው አመራር ሥራዎችን ማስኬድ፡፡ የተወሰነው ውሳኔ ፕሮግራሞችን መሰረዝ ሳያስፈልግ ተኪ አመራሮችን በቅርበት መደገፍ መሆኑ ስጋታችንን ከፍ ያደረገው ነበር፡፡ ከእነኚህና ሌሎች በርካታ ካጋጣሙን ተግዳሮቶች ለወደፊቱ ስራዎቻችን የሚያግዙ ብዙ ትምህርት የቀሰምንባቸው ሲሆን ሌሎች ያላሰብናቸው ብዙ ትሩፋቶች ጭምር አግኝተን አልፈናል፡፡

## II. የተገኘው ትምህርትና ትሩፋት

የ2014 ፈተና አሰጣጥ በተለየ አግባብ መስጠታችን በትምህርት ሥርዓቱ ላይ የደረሰውን ስብራት ለማረም የመጀመርያው እርምጃ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች በርካታ ትምህርት ሰጥቶናል ካሰብነውም ውጭ ትሩፋቶች አግኝተንበታል፡፡ በቀጣይ ለምናስባቸው ሌሎች የሪፎርም እርምጃዎችና መተግበር ለምንፈልጋቸው ጉዳዮች ልዩ እድል ፈጥሮልናል ማለት ይቻላል፡፡

**ትምህርት አንድ** ፡ ትልቅ አቅም ያለን መሆኑን በጥቂቱ እንድናይ ረድቶናል፡፡
ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻችን በአግባቡ ከተመሩ፣ ከቆረጡና ጥረት ካከሉበት ለየትኛውም ተልዕኮ ስኬት ያላቸው እምቅ አቅም ከፍ ያለ መሆኑን አሳይቶናል፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ አቅም ማስፋት ትላልቅ ጉዳዮችን መፈጸም የሚቻል መሆኑን ተረድተንበታል፡፡

**ትምህርት ሁለት**፡ መላው ህዝባችን ሲያማርርባቸው የነበሩትን ጉዳዮች መንግስት ለማረም ሲነሳ፤ ጥረት ሲያደርግ ድጋፍ እንደሚያገኝ በተጨባጭ አሳይቶናል፡፡ ማህበረሰቡ በባለፉት ዓመታት በፈተና አስተዳደር ያጋጠሙ ችግሮች መታረም እንዳለባቸው መጠየቅ ብቻ ሳይሆን ችግር የሚፈታ ተጨባጭ እንቅስቃሴ ከተደረገ በቻለው ሁሉ እንደሚደግፍ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም በቀጣይ እንደ አገር ህዝቡ በሚያማርርባቸው የተደራጀ ሌብነት፣ መልካም አስተዳደርና ፍትህ እጦት፣ የመንግስት አገልግሎት በእጅ መንሻ ማግኘት… ወዘተ ቁልፍ ችግሮች እንደዚሁም በትምህርት ሴክተር ሃሰተኛ ትምህርት ማስረጃና በትምህርት ላይ የሚደረግ ወንጀል ለማስተካከል ህዝቡን ከጎናችን ካሰለፍን እሩቅ በማይባል ጊዜ ውስጥ ትርጉም ባለው ደረጃ ውጤት ማስመዝገብ እንችላለን፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን በፈተናው ወቅት የፈተናውን ሂደት ለማወክና እንዳይሳካ ለማድረግ የሞከሩትን ሊተባበር ቀርቶ በሚገባ ታግሎ አስቁሟቸዋል፡፡  ትልቁ ትምህርት ከጥረት ውጭ ውጤት ማግኘትን የሚጠየፍ ማህበረሰብ አለ፡፡ መንግሥት ይህን ለማድረግ ጠንክሮ ከሰራ ከማህበረሰቡ ከፍተኛ ትብብር እንደሚያገኝ አሳይቶናል፡፡

**ትምህርት ሶስት** ፡ አገራችን ኢትዮጵያ የተከፈተባትን ጦርነት፣ መጋፈጥና ማለፍ ያለባት ፈተና የአንድ ግንባር ብቻ አይደለም፡፡ አሁን ባለንበት ዘመን ሁሉንም ትኩረታችን በአንድ ነጠላ ጉዳይ ላይ ብቻ በማድረግ የተሻለ ነገን መፍጠር አንችልም፡፡ ያሉትን ውስብስብ ችግሮች ሁሉም ባለበት መፍታት እንጂ ጠላቶቻችን በሚሰጡን አጀንዳ ላይ ብቻ ሁሉንም አቅማችንን በማዋል ጠንካራ አገር መገንባት አይታሰብም፡፡ ኢትዮጵያ ሉአላዊነቷንና የግዛት አንድነቷን እያስከበረችም በሌሎች ዘርፎች የላቁ ስኬቶች ማስመዝገብ ትችላለች፡፡

**ትምህርት አራት፡** በመጨረሻም ይህ የ2014 ፈተና አስተዳደር ተግዳሮትን ወደ አቅም በመቀየር ትምህርት የሰጠን ብቻ አይደለም፡፡ይልቅስ ካስቀምጥነው ፍትሃዊ የፈተና አስተዳደር ሥርዓት መፍጠር ግብ የተሻገሩ ትሩፋቶች አስገኝቷል፡፡

**ትሩፋት አንድ**፡ ኢትዮጵያዊያኖች አሁንም የተሳሰርንበትና የተጋመድንበት ጠንካራ ሶሻል ፋብሪክ ያለን መሆኑን

የዩኒቨርስቲ መምህራኖቻችንና ሌሎች ፈተና አስፈፃሚዎች ከተቋማቸውና ከሚሰሩበት ክልል ወጥተው ሥምሪት ሲሰጣቸው እንዴት ይቀበሉታል በቅርብ ዓመታት ያየናቸው አንዳንድ ክስተቶች ምን ዓይነት ጫና ያሳድራሉ ብሎ መጨነቅ የሚጠበቅ ነው፡፡ በተቃራኒው ያጋመደን እና አብሮ ያቆየን ኢትዮጵያዊ ማንነታችን ችግርን መቋቋም ብቻ ሳይሆን ጠላቶቻችን ከሚመኙልን በተቃራኒው

አሁንም ጠንካራ መሆኑን በተጨባጭ ማየት ተችሏል፡፡ የመቱ ዩኒቨርስቲ መምህር ደባረቅ ዩኒቨርስቲ ሂዶ ሰሜን ተራራን ጎብኝቶ የሰጠው ምስክርነት፣ የጎንደር ዩኒቨርስቲው መምህር ወለጋ ዩኒቨርስቲ ሲደርስ ተሰማኝ  ያለውና ግን ያጋጠመውን የገለፀበት እንደዚሁም በበርካታ ሌሎች አከባቢዎች በነበሩ የፈተና አስፈፃሚዎች ጉብኝት ወቅት የተሰሙ አስተያዬቶች ብዙ ትርጉም ያለው መልእክት የያዙ ናቸው፡፡

**ከመቱ ደባርቅ የሄደው** ፡ ደባርቅ ሲደርሰኝ ተጨንቄ ነበር፤ ብዝሃነት(ፑሉላሪት) ችግር ያለበት ነው ተብየ የመጣሁት፣ ትልቅ መስጊድ አይቻለሁ፣ በቋንቋዬ ብናገር የከፋው የለም እንግዳ ወዳድ ናችሁ …ፍቅር ናችሁ..

**ከጎንደር ወደ ወለጋ የሄደው 1** ፡ ወለጋ ፈታኝነት ደረሰኝ ስላቸው ነብስህ በሰላም ትረፍ ተባልኩ ፡ ቀናት አለፉ የሞት መድር የተባለልሽ ወለጋ የት ነሽ እላለሁ

**ከጎንደር ወደ ወለጋ የሄደው 2** ፡ ወለጋ አልሄድም እዛው ሞቶ አልቆ ለምን እሄዳለሁ ብየ ነበር…. አሞኝ ክሊኒክ በነፃ ታከምኩ.. የትም ህገወጥ አለ ህዝብን ግን አይወክልም…አየር ላይ ያለው ፖለቲካ ግን ብዙ አለያይቶናል.. የወለጋ ህዝብ ወርቅ ነው፤

**ትሩፋት ሁለት**፡ የሚኒስቴር መሥርያ ቤቱን ቅቡልነት መልሶ ለማግኘት የእድል በር የተከፈተበት ትሩፋት

እንደ አገር የመንግስት ተቋማት ቅቡልነት መውረድና አሰራራቸውን መጠራጠር እያደገ መምጣት ተቋማትም ተገማች ካለመሆናቸው ጋር ተዳምሮ ትምህርት ሚኒስቴር በባለፉት ዓመታት ከፈተና አስተዳደር ጋር ተገናኝቶ ባጋጠሙት ችግሮች ተማሪና ወላጅ ዘንድ የነበረው ቅቡልነት በእጅጉ ወርዶ ነበር ለማለት ያስደፍራል፡፡ የሚታሰቡ ሪፎርሞችን መጠራጠርና ከወሬ ባለፈ አትፈፅሙትም የሚለው ድምጽ እየጎላ መጥቶ ነበር፡፡ በዚህ በ2014 ፈተና አስተዳደር ትምህርት ሚኒስቴር፣ ክልል ትምህርት ቢሮዎችና ዩኒቨርስቲዎች በከፍተኛ ደረጃ ተቀናጅተው ከሌሎች በርካታ የመንግስት ተቋማት በተሰጠ ድጋፍ መንግስት የተናገረውን የሚያደርግና በከፍተኛ ብቃት መፈፀም እንደሚችል ያሳየበት ስለሆነ በቀጣይ የህዝቡን ድጋፍ ለሚሹ ሥራዎችና ቅቡልነት ያለው የሚታመን የትምህርት ሥርዓት ለመገንባት ወርቃማ እድልና ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

//////=====////////

# ክፍል ሶስት

## ሪፖርት የተደረጉ የፈተና ደንብ ጥሰቶችና እርምጃዎች

ፈተናው ከመስጣቱ ቀድሞ በመፈተኛ ማዕከላት እና ፈተናው በሚሰጥበት ወቅት የተለያዩ የደንብ ጥሰቶች ሪፖርት ተደርገዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 1. ተንቀሳቃሽ ስልክ ይዞ በመፈተኛ ክፍል ወይም በመፈተኛ ማዕከል ግቢ ውስጥ መገኘት ወይም መጠቀም

| ተቁ | የመፈተኛ ማዕከል | ሞባይል ይዞ የተገኘ ተፈታኝ ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1. | ጂማ ዋናው ግቢ | 03 | |
| 2. | ወራቤ | 01 | |
| 3. | ጅማ ቴክኖሎጂ ካምፓስ | 01 | አንድ ተማሪ ሁለት ሞባይል |
| 4. | አርሲ ዩኒቨርሲቲ አሰላ ካምፓስ | 01 | |
| 5. | አምቦ ዩኒቨርሲቲ ወሊሶ ካምፓስ | 01 | እህቱ ብር አምጥታለት ወደ በር ሄዶ የተያዘ፡፡ በፖሊስ ዶርሙ ሲፈተሽ የተገኘ |
| 6. | ቦንጋ | 02 | |
| 7. | AASTU | 05 | |
| 8. | ወሎ ዩኒቨርሲቲ ኮምቦልቻ ካምፓስ | 02 | |
| 9. | ደባርቅ የኒቨርሲቲ | 01 | |
| 10. | ቦረና ዩኒቨርሲርሲቲ | 01 | |
| 11. | ጅማ የግብርና ከምፓስ | 02 | |
| 12. | መዳወላቡ | 01 | |
| 13. | አምቦ ጉዳር ከምፓስ | 01 | |
| 14. | አምቦ ዩኒቨርሲቲ ወሊሶ | 01 | |
| 15. | ወለጋ ግምቢ ካምፓስ | 03 | |
| 16. | ኦዳ ቡልቱም | 01 | |
| 17. | አርሲ ዩኒቨርሲቲ | 05 | |
| 18. | ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ | 01 | |
| 19. | ወላይታ ሶዶ ዋና ግቢ | 01 | |
| 20. | ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ (ሆስፒታል) | 01 | |
| 21. | ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ | 05 | |
| 22. | ጂንካ ዩኒቨርሲቲ | 04 | |
| 23. | ዲላ | 02 | መልስ ከውጪ ስላክላቸው ነበር |
| 24. | ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ | 02 | |
| 25. | አዲስ አበባ አርክቴክቸር ካምፓስ | 01 | |
| 26. | ወሎ ኮምቦልቻ | 01 | |
| 27. | ሰመራ ዩኒቨርሲቲ | 01 | |
| 28. | ባህር ዳር ጥበበ ጊዮን | 01 | |
| 29. | ጅማ ዋና ግቢ | 01 | |
| 30. | በ40ምንጭ ኩልፎ ካምፓስ | 03 | መኝታ ክፍል የተገኘ |
| 31. | ወላይታ ዋናው ዩኒቨርስቲ | 01 | |
| 32. | ወላይታ ጦና ካምፓስ | 01 | |
| 33. | በ10/02/2015 ዓ/ም ዲላ ኦዳያ | 01 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ካምፓስ ውስጥ 01 | | |
| 34. | ጂግጅጋ ዩኒቨርሲቲ | 04 | |

ልዩ ማስታወሻ (ሞባይሎች የተገኙባቸው ቦታዎችና መንገዶች):-

- በጫማ ሶል ውስጥ ወይም ጎን ላይ በመስፋት
- በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች በመደበቅ
- በዳቦ፣ በቆሎ፣ በልብስ መካከል፣ ፀጉር ውስጥ አብሮ በመሠራት፣
- በፌስታል ቋጥሮ ወደ ጊቢ ውስጥ አርቆ በመወርወር ሲም ካርዱን ብቻ ይዞ በመግባት

## 2. ጫት እና ሌሎች አደንዛዥ እጾችን እንዲሁም አልኮል/አረቄ ይዞ መገኘት

በተለያየ መፈተኛ ማዕከላት ጫት፣ አደንዛዥ ዕጽና አደንዛዥ መድኃኒቶችን ይዘው የተገኙ አሉ፡፡ ለምሳሌ የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም ያለ ተፈታኝ በአጥር ሀሺሽ ሲቀበል፤ ወሎ ዩኒቨርሲቲ ኮምቦልቻ ከምፓስ ጫት ይዘው መጥተው፣ በ05/02/2015 ዓ/ም ባህር ዳር ፖሊ ካምፓስ 02 ተማሪዎች 02 ግማሽ ሊትር አረቄ ይዘው ወደ ዩኒቨርስቲው ሲገቡ ተይዘዋል፡፡

ስለሆነም ጫት እና ሌሎች አደንዛዥ እጾችን እንዲሁም አልኮል/አረቄ ይዞ የተገኙ ተፈታኞች ከፈተና የተሰረዙ ከመሆኑ ባሻገር የፌዴራል ፖሊስ ይዞ መገኘት/መጠቀም በወንጀልነት በሚያስጠይቁ ጉዳዮች ላይ ህጋዊ እርምጃዎችን በመውሰድ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

## 3. የጦር መሣሪያ እና ስለቶችን/ዱላ ይዞ መገኘት

በተለያየ ተቋማት የጦር መሣሪያ፣ ጥይት በቦርሳቸው ውስጥ የያዙ፣ ስለት/ዱላ ይዘው በመፈተኛ ማዕከል ላይ የተገኙ ተፈታኞች ተይዘው በፌዴራል ፖሊስ ህጋዊ ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በመፈተኛ ማዕከል ውስጥ የጦር መሣሪያ፣ ስለት/ዱላ ይዘው የተገኙ ሁሉ ከፈተና ታግደዋል፡፡ ለምሳሌ ድሬዳዋ 01 ተፈታኝ ስለት ይዞ በመገኘት፣ በመቅደላ አምባ ዩኒቨርስቲ ቱሉ አወሊያ ከምፓስ ዱላ የደበቁ ተፈታኞች፣

## 4. ፈታኞችን ወይም ሌሎች ተፈታኞችን በግል ወይም በቡድን ሆኖ የማስፈራራት

ፈታኝንም ይሁን ተፈታኝን በግልም ይሁን በቡድን በስነ ልቦና ጫና ውስጥ በመክተት ለመረበሽ በማሰብ የተደረገ ሪፖርትን መሠረት በማድረግ ከፈተና የመሰረዝ እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል፡፡

- በ08/02/2015 ዓ/ም ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጊሽ አባይ ካምፓስ ውስጥ 02 ተፈታኝ ተማሪዎች ከጎናቸው የተቀመጠችን 01 ሴት ተፈታኝ ተማሪ እንገልሻለን ብለው በማስፈራራታቸው በፖሊስ ተይዘው ከሁሉም ፈተና ተሰርዘዋል፡፡

- በ09/02/2015 ዓ/ም ወለጋ ሸምቡ ካምፓስ ውስጥ የተፈጥሮ ሳይንስ የጠዋት ተፈታኝ 02 ተማሪዎች ሲኮራረጁ የተያዙ ሲሆን የያዘቸውን መምህር ‹‹እናገኝሃለን በማለት ማስፈራራታቸው
- በ11/02/2015 በአዲስ አባባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከነበሩ ተፈታኞች በቡድን ሆነው ሌሎች ተፈታኞችን ማስፈራራት

## 5. ፈታኞችን አባረው ወይም አስፈራርተው በቡድን መኮረጅ

በማንኛውም ደረጃ በቡድን ሆነው ኩረጃ የፈጸሙ ተፈታኞች ፈተናቸው የሚሰረዝ ይሆናል፡፡

ለምሳሌ፡-

- አርባ ምንጭ የኒቨርሲቲ ነጭ ሳር ከምፓስ
  - ከጎፋ ዞን የመጡ የሳውላ ት/ት ቤት 295 የጅኦግራፊ ፈተና እና 99 የታሪክ ፈተና ፣ 97 የስነ ዜጋ ፈተና በድምሩ 491 በቡድን ኮርጀዋል፡፡ ፈተናቸው የሚሰረዝ ይሆናል፡፡
  - ጎፋ ዞን ሳውላ ከተማ አስተዳደር ዱዛ መለስ ዜናዊ ት/ቤት 08 ተፈታኞች የታሪክ ፈተና፣ 22 ተፈታኞች የስነዜጋ ፈተና፣ በቡድን ኮርጀዋል፡፡ ፈተናቸው የሚሰረዝ ይሆናል፡፡

- ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጥበበ ጊዮን ከምፓስ
  - በማህበራዊ ሳይንስ ምዕራብ ጎጃም ደጋ ዳሞት ወረዳ የመጡ የፈረስ ቤት ትምህርት ቤት 1155 መደበኛ ተፈታኞች ታሪክ፣ ጂኦግራፊ፣ ስነ ዜጋና አፐቲትዩድ ፈተናዎችን ፈታኞች ላይ በማመጽ፣ የጸጥታ አካላትን ጭምር እምቢ ብለው በክፍል ውስጥ በቡድን ከአንድ መፈተኛ ክፍል ወደ ሌላ መፈተኛ ክፍል ሁሉ እየሄዱ ፈተና ኮርጀዋል፡፡ ስለሆነም ፈተናቸው የሚሰረዝ ይሆናል፡፡
  - በማህበራዊ ሳይንስ ምዕራብ ጎጃም ዞን የፈረስ ቤት ትምህርት ቤት የግል 04 እና የማታ 84 ተፈታኞች ያለ ምንም የፈተና ደንብ ጥሰት የተፈተኑ በመሆናቸው ፈተናቸው በአግባቡ የሚታረምና ውጤት የሚገለጽ ይሆናል፡፡
  - ምዕራብ ጎጃም ዞን ወግዳድ ት/ቤት ከ93 መደበኛ ተፈታኞች 53 ተፈታኞች የታሪክ ፈተና፣ 01 ተፈታኝ በስነ ዜጋ የግል ኩረጃ አድርገዋል፡፡ ውጤታቸው የሚሰረዝ ይሆናል፡፡

- ምዕራብ ጎጃም አሹዳ ትምህርት ቤት ከተፈተኑት 255 ተፈታኞች 23 ተፈታኝ የታሪክ ፈተና፣ 19 ተፈታኝ የጅኦግራፊ የቡድን ኩረጃ ፈጽመዋል፡፡ ፈተናቸው የሚሰረዝ ይሆናል፡፡
- ምዕራብ ጎጃም ዞን ጣዕመ ትምህርት ቤት ከ323 መደበኛና 39 የማታ ከተፈተኑት መካከል 133 ተፈታኞች የአፕቲትዩድ፣ የታሪክ፣ የጂኦግራፊና የሲቪክስ ፈተናዎችን በቡድን ኮርጀዋል፡፡ ፈተናቸው የሚሰረዝ ይሆናል፡፡
- ምዕራብ ጎጃም ዞን ኮኪ ትምህርት ቤት 38 መደበኛ ተማሪዎች መካካል 08 ተፈታኞች የሲቪክስ ፈተና በቡድን ኮርጀዋል፡፡ ፈተናቸው የሚሰረዝ ይሆናል፡፡
- ምዕራብ ጎጃም ዞን መኮንን ሽንዲ ትምህርት ቤት ከ589 ተፈታኞች መካከል የሒሳብ 01፣ የታሪክ 434፣ የሲቪክስ 468 ተፈታኞች የቡድን ኩረጃ ፈጽመዋል፡፡ ፈተናቸው የሚሰረዝ ይሆናል፡፡
- ምዕራብ ጎጃም ዞን ሽንዲ ትምህርት ቤት ከ613 መደበኛ፣ የማታ 39 የግል 02 መካከል በታሪክ እና ስነ ዜጋ ላይ 23 መደበኛ የማታ 39 በቡድን ኮርጀዋል፡፡ ፈተናቸው የሚሰረዝ ይሆናል፡፡

- ዲላ ዩኒቨርሲቲ ሀሴ ዴላ ከምፓስ ከቡሌ ወረዳ የመጡ ከቡሌ ት/ቤት 06 በቡድን ሲኮርጁ ተይዘዋል፡፡ ፈተናቸው የሚሰረዝ ይሆናል፡፡
- ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ይባብ (ግሽ አባይ) ከምፓስ፡- ምስራቅ ጎጃም ዞን ቲሊሊ ት/ት ቤት 826 መደበኛ ተፈታኞች ታሪክና ስነ ዜጋ ፈተና ሲካሄድ በቡድን የኮረጁ ከመሆኑም ባሻገር መምህራንን ማስፈራራት፣ አቴንዳንስ በመቅደድ፣ መጠባባቂያ መልስ ወረቀቶችን መቅደድ፣ የጸጥታ ኃይልን አለመታዘዝና ለግጭት መገፋፋት፣ ፈታኞችን ከመፈተኛ ክፍል የማባረር ተግባር ፈጽመዋል፡፡ አባረዋል፡፡ ውጤታቸው የሚሰረዝ ይሆናል፡፡
- በ08/02/2015 ዓ/ም ወሎ ኮምቦልቻ ካምፓስ የከሰዓት የተፈጥሮ ሳይንስ ተፈታኝ የሆኑ 02 ተማሪዎች ሲኮርጁ ተይዘዋል፡፡
- በ02/02/2015 ዓ/ም ጀጅጋ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ፈታኞችን እያስገደዱ ለማሰራት ሲሞክሩ ፖሊስ በመፈተኛ በር ላይ ተመድቦ ፈተናው እንዲካሄድ አድርገዋል፡፡

## 6. አንፈተንም ብሎ በኃይል በማመጽ ፈተናውን ትቶ ከመፈተኛ ማዕከል በራስ ፈቃድ መሄድ

6.1. መቅደላ አምባ የኒቨርሲቲ መካነ ሰላም ማዕከል - በ30/01/2015 ዓ.ም ከምስራቅ ጎጃም ዞን የመጡ የደብረ ወርቅ ት/ቤት፣ የፈለገ ብርሃን ት/ት ቤት እና የታንጉማ ት/ቤት ተፈታኞች ማህበራዊ ሳይንስ ፈተና ከተመዘገቡ 2640 ተፈታኞች (ወ 1077

ሴ 1563) መካከል 928ቱ ለፈተና የተቀመጡ (ወንድ 386 ሴት 542) ሲሆን 1711ዱ (ወንድ 691 ሴት 1021) በፈቃዳቸው ፈተናውን ጥለው ሄደዋል፡፡

6.2. ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ -

| ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስ ተፈታኞች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተመደቡ | ለመፈተን የመጡ | ሳይመጡ የቀሩ | በፈቃዳቸው አንፈተንም ብለው የወጡ | በፈቃዳቸው ቀርተው የተፈተኑ |
| ደብረ ታቦር 1 | 9,027 | 8,040 | 987 | 4,107 | 3,933 |
| ደብረ ታቦር 2 | 8,089 | 7,401 | 688 | 3,249 | 4,207 |
| ድምር | 17,116 | 15,441 | 1,675 | 7,356 | 8,140 |

6.3. ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ከምፓስ ከተመደቡ 4334 ተፈታኞች መካከል 3887 ተፈታኞች የመጡ ሲሆን ከእነብሴ ሳር ምድር እና ከሁለት እጁ ይነሴ ወረዳዎች የመጡ 1211 ተፈታኞች አንፈተንም ብለው ወደ ቤተሰቦቻቸው ሄደዋል፡፡ በፈቃዳቸው ቀርተው የተፈተኑት 2676 ናቸው፡፡

6.4. ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፖሊ ከምፓስ ፈተና አንፈተንም በማለት 613 ተማሪዎች ከፈተና ውጭ ሆነዋል፡፡ በፕሬዝዳንቱ ምክር ቢደረግላቸውም ግቢውን ለቀው ወጥተዋል፡

## 7. አርፍዶ ወደ መፈተኛ ክፍል ለመግባት መሞከር

7.1. በፈተና ደንብ መሠረት ማንኛውም ተፈታኝ በማንኛውም ምክንያት ፈተናው ከተጀመረ ከ30 ደቂቃ በኃላ ወደ መፈተኛ ክፍል መግባት አይችልም፡፡ በ01/02/2015 ዓ/ም ከጠዋቱ 3፡47 ሰዓት ዲላ ዩኒቨርሲቲ አስ ዴላ ከምፓስ የሚፈተኑ 11 ተማሪዎች 47 ደቂቃ አሳልፈው ወደ ፈተና ክፍል ሊገቡ ሲሉ ሲፈተሹ 4ቱ ተማሪዎች የፈተና መልስ ይዘው የተገኙ ሲሆን ሲጣራ ከዶርማቸው ውስጥ 2ቱ ተማሪዎች 2 ሞባይል የተገኘ ሲሆን 3ኛው ተማሪ ሲም ካርዱን በሞባይላቸው ውስጥ አስገብቶ ስለነበር ሞባይሉ ሲፈተሽ ከኦሮሚያ ክልል አምቦ ዩኒቨርሲቲ 1ኛ ዓመት ተማሪ የሆነው ሙሴ ወልዴ የተባለ ግለሰብ በሞባይሉ ለ3ቱ ተማሪዎች መልስ ልኮላቸው ተገኝቷል፡፡ የተላከላቸው መልስ

ይትክክለኛው የ2014 ፈተና ሳይሆን ያለፈ ፈተና ነበር፡፡ የፈተና ውጤታቸው የሚሰረዝ ይሆናል፡፡

7.2. በ09/02/2015 ዓ/ም አ/አበባ ሳይንስ እና ቴክኖሎጅ ዩኒቨርሲቲ የከሰዓት የተፈጥሮ ሳይንስ ተፈታኝ የሆኑ 02 ተማሪዎች በመኝታ ክፍላቸው ውስጥ ተኝተው ፈተናው ከተጀመረበት ሰዓት 45 ደቂቃ አሳልፈው በመምጣታቸው ፈተናው አልፏቸዋል፡፡

## 8. ከመፈተኛ ማዕከል አጥር ዘሎ መውጣት/መሞከር ወይም ተደብቆ ወጥቶ መጠጥ ጠጥቶ ለመግባት መሞከር

8.1. በ30/01/2015 ዓ/ም ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ፈተናው በአግባቡ እንዳይከናወን ሲቀሰቅሱ የነበሩ በጥቆማ 11 ተማሪዎች ተለይተው ከፈተና ውጭ እንዲሆኑ ተወስኗል፡፡

8.2. ጎንደር ጠዳ ካምፓስ የሚፈተኑ 07 ተማሪዎች ፈተናውን 45 ደቂቃ ጨርሰው በመውጣት በአጥር ዘለው ሲወጡ በፖሊስ ተይዘዋል

8.3. ወሎ ኮምቦልቻ - 01 ተማሪ አጥር ዘሎ ሲወጣ ተይዞ ሳይፈተን ቀርቷል

8.4. ደብረ ማርቆስ ቡሬ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በ01/02/2015 ዓ/ም በነበረው ረብሻ ምክንያት በአጥር ዘለው ከግቢው የወጡ 95 ተማሪዎች ወደ ቤተሰቦቻቸው ሄደዋል፡፡ በ02/02/2015 ዓ/ም ሲረብሹ የተያዙ 04 ተፈታኝ ተማሪዎች በፖሊስ ተይዘው ፖሊስ ጣቢያ ታስረዋል፡፡ በድምሩ 99 ተማሪዎች የእለቱን ፈተና አልተፈተኑም፡፡

8.5. ደብረ ማርቆስ ቡሬ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በ01/02/2015 ዓ/ም በነበረው ረብሻ ምክንያት በአጥር ዘለው ከግቢው የወጡ 95 ተማሪዎች ወደ ቤተሰቦቻቸው ሄደዋል፡፡ በ02/02/2015 ዓ/ም ሲረብሹ የተያዙ 04 ተፈታኝ ተማሪዎች በፖሊስ ተይዘው ፖሊስ ጣቢያ ታስረዋል፡፡ በድምሩ 99 ተማሪዎች የእለቱን ፈተና አልተፈተኑም፡፡

8.6. ደባርቅ ዩኒቨርስቲ ከሚፈተኑ ተማሪዎች ውስጥ 02 ተፈታኝ ተማሪዎች ከጊቢው ወጥተው መጠጥ ጠጥተው ሊገቡ ሲሉ በፖሊስ ተይዘው ጣቢያ ታስረዋል፡፡

## 9. ወደ መፈተኛ ክፍል ሲገቡ አንፈተሽም ብሎ ከፈታሾች ጋር መጋጨት

30/01/2015 ዓ.ም ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ የከሰዓት በኃላ ፈተና ተፈታኝ ተማሪዎች እየተፈተሹ ሲገቡ አንፈተሽም ዝም ብለን መግባት አለብን በማለት በቡድን የጮሁ ቢሆንም በፀጥታው ኃይል ተፈትሸው እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

## 10.ለሌሎች መፈተን

10.1. ጅግጅጋ 1 ግለሰብ -ለአባቱ ለመፈተን - 01/0215

10.2. ጅግጅጋ፦ 05 ተማሪዎች ተማሪ ያልሆኑ ተይዘዋል፣ 02 ግለሰቦች በሌላ ሰው ባጅ ሲገቡ ተይዘዋል፣

10.3. በ08/02/2015 ዓ/ም ጅጅጋ ዩኒቨርስቲ ውስጥ 01 ግለሰብ አድሚሽን ካርድ አመሳስሎ በማሰራት ለአባቱ ፈተና ሲፈተን ተይዞ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውሎ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተልኳል፡፡

10.4. በ09/02/2015 ዓ/ም ጅጅጋ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ለዘመዶቻቸው ሊፈተኑ የነበሩ 10 ተማሪ የፈዘዘ ፎቶግራፍ ያለበት አድሚሽን ካርድ ይዘው ሲገቡ ተይዘዋል፡፡

## 11.ፌዴራል ፖሊስ ከግቢ ይውጣልን ብሎ ብሎ መረበሽ

ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ፌደራል ፖሊስ ከግቢው ይውጣልን ልዩ ሃይል ነው መፈተሽ ያለበት በሚል ረብሻ የፈጠሩ ሲሆን ዋነኞቹ ተይዘው በህግ እንዲጠየቁ በሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡

## 12.ተሰብስቦ ከፍተኛ ድምጽ እያሰሙ መጮህ/መጨፈር አልፎ አልፎም ሲጋራ ማጨስ

12.1. አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማታ ሲጨፍሩ 02 የመስኮት መስታወት ሰብረዋል፡፡

12.2. በ03/02/15 አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አራት ኪሎ ከምፓስ/ኮሌጅ ተፈታኞች ማታ ማታ መጮህና ሲጋራ ሲያጨሱ ተይዘዋል፡፡

12.3. በ03/02/15 አአዩ ሰፈረ ሰላም ከምፓስ - ተማሪዎች የመጮህ እና ጎበዝ ተማሪዎችን የመረበሽ ሁኔታ ነበር፡፡

12.4. በ06/02/2015 ዓ/ም ስቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በ02 ብሎክ ውስጥ የተመደቡ ተማሪዎች ማታ ላይ ባልታወቀ ሁኔታ ጩሀት አሰምተዋል፡፡

12.5. በ06/02/2015 ዓ/ም ወልዲያ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሚፈተኑ የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች ማታ ላይ በከፍተኛ ድምጽ አየተሳደቡና እየጮሁ ነበር፡፡

12.6. በ10/02/2015 ዓ/ም ወለጋ ዩኒቨርሲቲ ነቀምት ከምፓስ 02 ክፍል ውስጥ ሲፈተኑ የነበሩ ተማሪዎች አመመን በሚል ጩኸት ያሰሙ ነበር፡፡ ፈተናውን በሰላም ጨርሰዋል፡፡

## 13.የመልስ ወረቀት ሳያስረክቡ ይዞ ለመውጣት መሞከር

ዲላ ዩኒቨርሲቲ 04 ተማሪዎች የመልስ ወረቀት በካልሲያቸው ይዘው ሊወጡ ሲሉ ተይዘዋል፡፡

## 14.ፈታኞችን እና ፖሊስን በአስጸያፊ ስድብ መሳደብ

14.1. በ10/02/2015 ዓ/ም ባህርዳር ፖሊ ካምፓስ 03 ተማሪዎች መምህር መሳደባቸው

14.2. በ10/02/2015 ዓ/ም ቀብሪደሃር ዩኒቨርስቲ 01 ተማሪ የጥበቃ ሰራተኛን ሲሰድበው ጥበቃው ተማሪውን በመምታቱ በጊቢው ውስጥ የነበሩ ተማሪዎች ለምን ትመታዋለህ በማለት ድንጋይ በመወርወር ጥበቃውን ሲፈነክቱት የክልሉ አድማ ብተና ፖሊስ አባሎች በቦታው ደርሰው ለማረጋጋት ቢሞክሩም የፖሊስ አባሎችን በመስደብ ሲረብሹ ፖሊስ 01 አስለቃሽ ጭስ ወደ ተማሪዎች በመተኮስ ረብሻውን አረጋግተው ለጊዜው 04 ተማሪዎች በቁጥጥር ስር አውለዋል፡፡

## 15.የፈተና ወይም የመልስ ወረቀት ቀድዶ ጥሎ መውጣት/መረበሽ

በ01/02/2015 ዓ/ም እንጅባራ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የከሰዓት ፈተና ላይ 01 ተማሪ የፈተና ወረቀት በመቅደድ ለረብሻ ለማነሳሳት ሲሞክር በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውሏል፡፡

## 16.በዩኒቨርሲቲ ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ

16.1. ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የመኝታ ቤቶች መስተዎት መስበር፣ ወንበሮችን መስበርና ፍራሾች መቅደድ እንዲሁም ወንበሮችና የመጸዳጃ ቤት ዕቃዎች ላይ የመሰባበር ጉዳት የደረሰ መሆኑ

16.2. በ08/02/2015 ዓ/ም ባህር ዳር ጥበበ ጊዮን ካምፓስ የተማሪዎች ክፍል ውስጥ 01 የመስኮት መስታወት የሰበረ 01 ተማሪ በፖሊስ ተይዟል፡፡

16.3. በ10/02/2015 ዓ/ም ከምሽቱ 1:00 በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ዩኒቨርሲቲ የሚፈተኑ ከግንጪ፣ ከቡራዩና ከሚኒሊክ ትምህርት ቤቶች የመጡ ተማሪዎች ጭፈራ ሲጨፍሩ ከቆዩ በኂላ ባልታወቀ ምክንያት ድንጋይ መወራወር ጀምረው የካፌ የበር እና የመስኮት መስታወት፣ ወንበር እና ጠረጴዛ መስበራቸው፣ የዶርም ፍራሽ መቅደድ፣ ረብሻው እስከ ምሽቱ 4:00 ሰዓት ቀጥሎ የፌደራል ፖሊስ እና የአዲስ አበባ ፖሊስ አባሎች በጋራ በመሆን እንዲረጋጉ አድርገዋል፡፡ አራት ፖሊስ አባላት በድንጋይ ተመተው ቆስለዋል፡፡ አንድ ተፈታኝ በድንጋይ ተመቷል፡፡ በ11/02/2015 ላይ አንድ ተፈታኝ ጭንቅላቱ ተፈንክቷል፡፡

በዚህ ሂደት የተሳተፉ በተለይም ፈተና ካጠናቀቁ በኃላ የረበሹ 160 ተፈታኞች በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡

## 17.አሉባልታዎችን ማውራት

- እንጅባራ ዩኒቨርስቲ 01 ተፈታኝ የሙስሊም እምነት ተከታይ የሆነ ሙስሊሞች በመርፌ እየተወጉ እየተገደሉ ነው እያለ ሲያወራ ተይዟል፡፡
- መንግስት ከፈተና በኃላ ወደ ጦርነት በግድ ሊወስደን ነው የሚል አሉባልታ ማውራት

## 18.በፈታኞች የተፈጸመ

18.1. ሳያስፈቅዱ መቅረት

በ10/02/2015 ዓ/ም 6 ኪሎ ዋናው ዩኒቨርስቲ የከሰዓት ፈተና ላይ 01 መምህር ሳያስፈቅድ አመመኝ ብሎ ከጊቢው ወጥቶ ከሄደ በኋላ የመጨረሻው ፈተና እስከሚያበቃ ድረስ አልተመለሰም፡፡

18.2. አርፍዶ መምጣት

18.3. የመልስ ወረቀት ከተማሪ ከተረከቡ በኃላ መጣል

- በ08/02/2015 ዓ/ም በአ/አበባ ኮተቤ ኮሌጅ በአንድ ክፍል ውስጥ 37 ተማሪዎች ተፈትነው እንደጨረሱ ፈታኙ ለሱፐርቫይዘሩ ለማስረከብ የፈተና ወረቀቱ ሲቆጠር የ08 ተማሪዎች የፈተና ወረቀት የጠፋ ሲሆን እስከ ምሽቱ 5፡00 ሰዓት ቢፈልጉም ሊያገኙት ባለመቻላቸው መምህር አልሰን ይሁን አንዷለም የተባለው ፈታኝ ጥፋተኛ በመሆኑ ቃለ ጉባኤ ተይዞ ከፈታኝነት ውጭ ሆኖ ፖሊስ ጣቢያ እንዲታሰር ተደርጓል፡፡ እነኚህ 8 የፈተና መልስ መስጭያ ወረቀቶቹ በተደረገው ጥብቅ ፍተሻ በቆሻሻ ማስቀመጫ ውስጥ ተጥለው ተገኝተዋል፡፡

- በአዲስ ምልስ ወረቀት ላይ የተማሪን ምልስ መሙላት፡- ባህር ዳር ፖሊ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ዶ/ር መኳንት ሽፈራው የተባሉ የጅማ ዩኒቨርስቲ መምህር የሆነ ፈተናውን ከፈተነ በኂላ ለአንድ ተማሪ ፈተና ሰርቶ ለተማሪው የተሰጠውን የፈተና ወረቀት ወንበር 3 ስር ጥሎ፤ በርክክብ ወቅት 01 የፈተና ወረቀት በመጥፋቱ የጠፋውን ወረቀት ከፖሊስ ጋር ሲፈልጉት ቆይተው እንዴት ሊጠፋ ቻለ በማለት ዶክተሩ ደብቆ ይዞት የነበረው ሪዘርቭ መልስ መስጫ ወረቀት ላይ መልስ የተሰራበትን ወረቀት ከኪሱ ውስጥ አውጥቶ ሲሰጥ እጅ ከፈንጅ በፖሊስ ተይዞ እየተጣራ ይገኛል፡፡ 30/01/2015

18.4. የፈተና መልስ መስጫ ወረቀቶችን ያለ ሰዓት ቀድሞ መውሰድ

- ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሰላም ከምፓስ ከ18 መፈተኛ ክፍሎች ላይ
- በ01/02/2015 ዓ/ም 6 ኪሎ ዋናው ካምፓስ ላይ ፈተናው ሊያልቅ 15 ደቂቃ ሲቀረው ፈታኙ አስገድዶ ፈተናችን ቀምቶናል በሚል ቅሬታ እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡

## 19.በፖሊስ አባላት የተፈጸሙ

19.1. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቢሾፍቱ ካምፓስ፡- ፈተና አጅበው ወደ ቢሾቱ ካምፓስ ከሄዱት የፌደራል ፖሊስ አባሎች መካከል FP 29858 ሳጅን ብሩክ ለማ ሽፈራው የተባለ የፀረ-ሽብር ፖሊስ መምሪያ አባል የሆነው በ03/02/2015 ዓ/ም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት አካባቢ ከተመደበበት ቢሾፍቱ ካምፓስ ካልሲ ልግዛ ብሎ ወጥቶ በ04/02/2015 ዓ/ም ከረፋዱ 5፡

30 ወደ ስራው የተመለሰ ሲሆን አባሉ ለምን አድሮ እንደመጣ ተጠይቆ ቤተሰቦቼ ተጣልተው አደጋ ሊደርስ ይችላል ብዬ ለማስማማት ሄጀ ነው ብሏል፡፡

19.2. በ06/02/2015 ዓ/ም አምቦ ዋናው ዩኒቨርስቲ ውስጥ፡-

- FP 44050 ም/ሳጅን አዲሱ አዳምነው አመዱ የተባለ የአድማ ብተና ፖሊስ መምሪያ አባል የሆነ ከአዲስ አበባ ፈተና አጅቦ የሄደ እና አስተባባሪ ተብሎ የተመደበ አባል እና
- FP 64349 ኮንስታብል ሃይሌ መብራቱ ሃይሉ የፀረ-ሽብር አባል እነዚህ 2ቱ አባሎች ለተማሪዎች ስልክ ሰጥተው ሲያስደውሉ በዙሪያ በተመደቡ ፈታሽ የፌ/ፖሊስ አባሎች ተይዘዋል፡፡
- በ09/02/2015 ዓ/ም ከቀኑ 11፡00 ሰዓት አርባ ምንጭ ነጭ ሳር ካምፓስ ውስጥ ከአዲስ አበባ ፈተና አጅቦ የሄደ FP 57978 ረ/ሳጅን ብርሃኑ ገ/ማሪያም ቀልባሪ የተባለ የአድማ ብተና መቆጣጠሪያ ፖሊስ መምሪያ አባል እቃ ገዝቼ ልምጣ ብሎ አስተባባሪው ፈቅዶ ሳይመጣ በመዘግየቱ ስልክ ተደውሎ ሲጠራ አልመጣም አድሬ ነው ምመጣው ብሎ በራሱ ፈቃድ አድሮ በ10/02/2015 መምጣቱ
- በ10/02/2015 ዓ/ም ጅማ እርሻ ካምፓስ ፈተና አጅቦ የሄደ FP 29676 ዋ/ሳጅን ታደሰ ተሾመ ሚኖታ የተባለ የአድማ መቆጣጠሪያ መምሪያ አባል የሆነው ያለቅርብ አመራሩ ፈቃድ ጥርናፌ ስቶ አድሯል በ11/02/2015 ዓ/ም ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ገብቷል፡፡
- በ10/02/2015 ዓ/ም ጅማ ዋናው ካምፓስ ውስጥ ፈተና ከአዲስ አበባ አጅቦ የሄደ FP 44104 ሳጅን አባይነህ ጭናሾ ቱመአ የአድማ መከላከል ፖሊስ መምሪያ አባል የሆነው፡- -ሳያስፈቅድ ከቀኑ 9፡30 ሰዓት እስከ ምሽቱ 1፡00 ሰዓት ድረስ ጥርናፌ ስቶ አምሽቶ መጥቷል፡፡

## ክፍል አራት

## ያጋጠሙ ችግሮች ቀጣይ አቅጣጫዎች

በፈተናው ሂደት ላይ የተለያየ ችግሮች አጋጥመዋል። ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 1. የመሻገሪያ ድልድይ መደርመስ

ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ከዋናው ግቢ ወደ ቴክኖሎጂ ግቢ መሻገሪያ ድልድይ ተፈታኞች ወደ መፈተኛ ክፍል ተሻግረው ለመግባት ለፍተሻ በድልድዩ ላይ እያሉ ተደርምሷል። በአጠቃላይ 451 ተፈታኞች ላይ ጉዳት ደርሷል (ህክምና ማዕከል የገቡ)። ከነዚህም መካከል 412 ቀላል ጉዳት ደርሶባቸው የህምና እርዳታ ተደርጎላቸዋል። 38 ተፈታኞች ከመካከለኛ እስከ ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው እስከሁን ህክምና ላይ ይገኛሉ፤ 01 የህይወት መጥፋት አደጋ አጋጥሟል።

በዚህም ምክንያት ዋናው ግቢ የተመደቡ 14,415 ተፈታኞች መካከል ለፈተና የመጡት 13,665 (750 የቀሩ) ሲሆኑ 13,665 የማህበራዊ ሳይንስ ተፈታኞች በተፈጠረው አደጋ ምክንያት እንግሊዘኛና ሂሳብ ፈተና አልተፈተኑም። ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ከምፓስ ከተመደቡ 7350 ተፈታኞች መካከል የቀሩ 382 ሲሆኑ ለፈተና የመጡ 6,968 ተፈታኞች በተፈጠረው አደጋ ምክንያት እንግሊዘኛ ብቻ አልተፈተኑም። ስለሆነም በአጭር ጊዜ የምሰጠውን ፈተና የሚፈተኑ ይሆናል።

### 2. የመንገድ ጉዞ ላይ ያጋጠሙ የትራፊክ አደጋዎች

- ኦሮሚያ ላይ ከምስራቅ አርሲ ሲሬ ወረዳ ወደ ኦዳ ቡልቱም መፈተኛ ጣቢያ ሲጓዙ 06 ተፈታኞች የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል።
- ከምዕራብ ሀራርጌ ከሸኔ ዱጎ ወረዳ ወደ ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ሲጓዙ በደረሰው የመኪና መገልበጥ አደጋ 03 ቀላልና 03 ከባድ በድመሩ 06 አደጋ በተፈታኞች ላይ ደርሷል።
- ከድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ወደ ምዕራብ ሀራርጌ ገለምሶ ወረዳ ሲጓዝ የነበረ መኪና ተገልብጦ 3 ተፈታኞች ላይ ከባድ እና የ01 ተፈታኝ የህይት መጥፋት አደጋ ደርሷል።
- ሁለት የመኪና አደጋ በጅማ ዞን የተከሰተ ቢሆንም በተፈታኞች ላይ ጉዳት አላደረሰም።
- ከምዕራብ አርሲ ከናንሰቦ ወረዳ ወደ መዳወላቡ ዩኒቨርሲቲ ሲጓዝ የነበረ መኪና ተገልብጦ በ03 ተፈታኞች ላይ ቀላል ጉዳት ደርሷል።

ልዩ መስተወሻ:- በ04/02/2015 ዓ/ም ደባርቅ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የተፈጥሮ ሳይንስ ተፈታኝ የሆኑ 16 ተማሪዎች መኪና ከማይገባበት ቦታ በእግራቸው ተጉዘው ጠዋት ላይ ወደ ዩኒቨርስቲው ገብተዋል፡፡

## 3. የተፈታኞችና የፈተና አስፈጻሚዎች መታመም

- ጅንካ ዩኒቨርስቲ ውስጥ 01 ሴት ተማሪ በውርጃ ምክንያት 01 ተማሪ በከፍተኛ የጨጓራ ህመም ምክንያት ፈተናውን አልተፈተኑም
- በ01/02/15 እራስን ስቶ መውደቅ - ባህዳር ዘንዘልማ 01 ተፈታኝ
- አአዩ ጥቁር አንበሳ 01 ተማሪ በትርፍ አንጀት ህመም አልተፈተነም
- ደባርቅ ዩኒቨርሲቲ ታመምን በሚል በቡድን ሆኖ የመጮህ
- ቦረና ዩኒቨርሲቲ በጭንቀት መንፈስ በመታመም የመውደቅና የመጮህ
- አምቦ ጉደር ካምፓስ አንድ ተፈታኝ በልብ ህመም ምክንያት በፈተና ላይ እያለ ታሞ ሐኪም ቤት ሄዶ ህይወቱ አልፏል፡፡
- ወልዲያ 02 ተፈታኞች በጭንቀት ምንፈስ ታመው ሲጮሁ ከፈተና ወጥተዋል
- በ10/02/2015 ዓ/ም አ/አበባ 5 ኪሎ ካምፓስ የከሰዓት ተፈታኝ ተማሪ የሆኑ 05 ተማሪዎች በጭንቀት ምክንያት ታመው አልተፈተኑም፡፡
- ደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ የመጣ ፈታኝ መምህር በአንጀት መታጠፍ ታሞ ኦፕራሲዮን ሆኖ ህክምና ላይ ይገኛል፡፡
- በ10/02/2015 ዓ/ም አ/አበባ 5 ኪሎ ካምፓስ የሚፈተኑ አንዳንድ ተማሪዎች በጭንቀት መንፈስ በመታመማቸው ወደ ህክምና ተልከዋል፡፡
- ጅማ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ 20 የሚሆኑ ተማሪዎች በጭንቀት ህመም ምክንያት መጮሃቸው
- በ11/02/2015 ዓ/ም አርሲ አሰላ ጤና ካምፓስ ውስጥ 08 ተማሪዎች በጭንቀት መንፈስ እየጮሁ ከፈተና ክፍል እየወጡ እየገቡ ፈተናውን ተፈትነዋል፡፡ •
- በ11/02/2015 ዓ/ም ጅማ ቴክኖሎጅ ካምፓስ 10 ተማሪዎች በፈተና ጭንቀት ታመው ከመፈተኛ ክፍል ውስጥ እየወጡ እየገቡ 09 ተማሪዎች ሲፈተኑ 01 ተማሪ አልተፈተነም፡፡

ስለሆነም በህመም ምክንያት ያልተፈተኑትን ተፈታኞች በአጭር ጊዜ በቀጣይ ዙር እንዲፈተኑ ይደረጋል፡፡

### 4. ወደ መፈተኛ ማዕከል ከገቡ በኃላ የወለዱ ተፈታኞች (ወሊድ)

| ተቁ | የተፈታኝ ስም እስከ አያት | አድሚሽን ካርድ ቁጥር | መፈተኛማዕከል (ዩኒቨ/ከምፓስ) |
|---|---|---|---|
| 1 | ማርታ ገብሬ ሚደቅሶ | 1045467 | AASTU |
| 2 | ሳምራዊት ያጉ | 0787047 | AASTU |
| 3 | ፋሲካ በላይ | 0565817 | Adama STU |
| 4 | ዛሊካ ሻዮቾ ሱሌ | 0560492 | Adama STU |
| 5 | ብርሃኔ ባልቻ አብዲ | 0580674 | Ambo - Hachalu |
| 6 | ብርቱኳን ተመስገን ደምሴ | 0460978 | Ambo - Hachalu |
| 7 | ገነት ኩመሳ ጀመማ | 5531977 | Ambo - Woliso |
| 8 | Seida Hasan Beriso | 0892857 | Arsi - Agricultur |
| 9 | Sadiya Kassim Muhammed | 0892846 | Arsi - Agricultur |
| 10 | ሀና አዳቻ በየነ | 0568601 | Arsi - Bussines |
| 11 | ሰፊያ ቱፋ ዋሾ | 0313776 | Arsi - Health |
| 12 | ጌጤ ጌቱ ፈለቀ | 9795521 | Arsi - Health |
| 13 | Kabale Konso Galgalo | 0343293 | Borana University |
| 14 | Daki Doyo Halake | 0344837 | Borana University |
| 15 | Kabale Bonaya Jllo | 1125627 | Borana University |
| 16 | ትዕግስት ኢሳያስ ጎባሮ | 0832087 | Dilla - Hasdelela |
| 17 | Tigst Esayas Gobaro | 0832087 | Dilla - Hasdelela |
| 18 | ማርእሼት ማሞ ቦኤ | 0831102 | Dilla - Odayyaa |
| 19 | ነፃነት ገ/ህይወት | 0796191 | ECSU |
| 20 | ቃልኪዳን ታደሰ | 0796119 | ECSU |
| 21 | ፈለግ በሬ ማለዳ | 0216954 | Gondar - CHMS |
| 22 | አስቴር ኤፍሬም ግሰሙ | 0279145 | Gondar - CHMS |
| 23 | ፈለግ በሬ ማለዳ | 0276954 | Gondar - CHMS |
| 24 | ኒማን ሹግሪ እስማኤል | 0609871 | Jgjiga |
| 25 | ኒማ | 0609871 | Jgjiga |
| 26 | Gutame Beyene Adal | 1084008 | TVTI |
| 27 | Mulunesh Abate Ababo | 0869957 | Wolayta Sodo - Dawuro |
| 28 | Aselefech Kapo Bolie | 1092317 | Wolayta Sodo - Dawuro |
| 29 | ነጃት ከድር | 0236272 | Wollo - Kombolcha |
| 30 | አህመድ ሰይድ ይመር | 0247076 | Wollo - Kombolcha |
| 31 | ሉባባ አህመድ ሙሀሙድ | 0237812 | Wollo - Kombolcha |
| 32 | ዘለቀው አያሌው ጀማል | 0237998 | Wollo - Kombolcha |
| 33 | ደራርቱ ሙሳ ሀጂ | 0180577 | Wollo - Kombolcha |

| ተቁ | የተፈታኝ ስም እስከ አያት | አድሚሽን ካርድ ቁጥር | መፈተኛማዕከል (ዩኒቨ/ከምፓስ) |
|---|---|---|---|
| 34 | ሶፍያ ቱፋ ዋሾ | 0313776 | ሜራሮ |
| 35 | ጌጤ በቀለ | 0453792 | |
| 36 | ጫልቱ ታደሰ አያና | 0995694 | |
| 37 | ሮቤል ገሰሰ አያና | 0994895 | |
| 38 | Bereket Abera | 1189959 | Wachamo - Hospital |
| 39 | Getnesh Landero Gorema | 0703419 | Wachamo - Hosana |
| 40 | Muale Keru Kedir | 0751414 | Worabe |
| 41 | Amarech Asfaw Chemero | 1087752 | Hawassa - CHMS |

ስለሆነም በወሊድ ምክንያት ላልተፈተኑት በአጭር ጊዜ እንዲፈተኑ ይደረገል፡፡

## 5. በተፈታኞችና በፖሊስ መካከል ግጭት

በደብረ ታቦርዮኖቨርሲቲ 05 ፈታኝ መምህራን ላይ ጉደት የደረሰ ሲሆን በአብዛኞቹ ፈታኝ መምህራን ላይ ከፍተኛ የመረበሽና የስነ ልቦና ጫና ደርሷል፡፡ የአንድ ተፈታኝ ህይወት አልፏል፡፡

AASTU በ11/02/2015 ዓ/ም ከግንጪ እና ቡራዩ አካባቢ ተፈታኞች አካባቢ የመጡ ተፈታኞች በመንፈስ ጭንቀት እየወደቁ እየጮሁ ከክፍል እየወጡ እየገቡ ፈተናውን ከጨረሱ በኋላ ማታ የጀመሩትን ረብሻ እንደገና ቅስቀሳ በማድረግ ‹‹የፈተና መልስ ለአዲስ አበባ ነዋሪ ተማሪዎች ተሰጥቷል›› በሚል እርስ በእር ግጭት ፈጥረው ሲረብሹ የአድማ ብተና አባሎች አስለቃሽ ጭስ በመተኮስ እንዲበተኑ ተደርጓል፡፡ ፖሊስ በሁከቱ ላይ እጃቸው አለባቸው ያላቸውን 162 ተጠርጣሪ ተማሪዎችን በቁጥጥር ስር አውለው ምርመራውን በማጣራት ላይ ይገኛሉ፡፡

## 6. በተፈታኞች መካከል የቡድን ፀብ

i. ቀብሪደሃር ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እርስ በርስ ድንጋይ የመወራወር እና መስታወት ለመስበር ሙከራ ነበር፡፡ 01/02/15

ii. በ10/02/2015 ዓ/ም ቀብሪደሃር ዩኒቨርስቲ 02 ተማሪዎች ተጣልተው ግርግር ሊፈጥሩ ሲሉ ፖሊስ አረጋግቶታል፡፡

## 7. የተሳሳተ መረጃ (የገለጻ ችግር)

i. ጂንካ ዩኒቨርሲቲ ወደ ዩኒቨርሲቲ ለፈተና አትሂዱ መንግስት ወደ ውትድርና ሊያስገባችሁ ነው የሚል አሉባልታ ወሬ ማውራት

ii. በ11/02/2015 ዓ/ም ዋቻሞ ዱራሜ ካምፓስ ውስጥ 01 ተማሪ የፈተና ጥያቄው ሳይሰጠው በመልስ መስጫው ወረቀት መልስ ሲሰራ ሌሎች ተማሪዎች መልስ የተሰጠው መስሏቸው ተማሪዎች በመንጫጫታቸው መምህራን አረጋግተው ተማሪውን ለብቻው እንዲፈተን አድርገውታል፡፡

## 8. የፈተና ሽራ ላይ መግለጫና የውስጥ የታሸገ ፖስታ መግለጫ መለያየት

i. ደብረ ብርሃን አንድ ጣቢያ - እንግሊዘኛና ባዮሎጂ

ii. ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ዋና 16 ጣቢዎች - ፊዝክስና ሲቪክስ

iii. ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ክምፓስ - አንድ ጣቢያ - እንግሊዘኛና ባዮሎጂ

iv. አምቦ ጉዳር ክምፓስ - እንግሊዘኛና ስነ ዜጋ

በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ ተፈታኞቹ ዘግይተው የተፈተኑ በመሆኑ በተዋረድ ያለው የትምህርት መዋቅር በሚያመጠው የውሳኔ ሐሳብ መሠረት ከፊዝክስ ፈተና ጋር ያለው ጉዳይ የሚታይ ይሆናል፡፡

## 9. ከፈተና ጥያቄ ዝግጅት አንጻር

### ከተዘጋጁ 13 ፈተናዎች እና 312 ቡክሌት ኮዶች መካከል

i. የታሪክ ፈተና ላይ በአንድ ኮድ ላይ አንድ ቁጥር ተደግሟል - 39/39

ii. የኬምስትሪ ፈተና ላይ በአንድ ኮድ ላይ (ኮድ 112) አራት ጥያቄዎች ተደግመዋል - እነዚህ ችግሮች በወቅቱ ተፈተዋል፡፡

## ክፍል አምስት

## ምስጋናና ማጠቃለያ

**10.ምስጋና**

ፈተናውን በማዘጋጀትና በማስፈተን ሂደት ላይ የተሳተፉትን የተለያዩ አካላትን ከልብ ማመስገን የሚገባ መሆኑ እሙን ነው፡፡ በዚሁ መነሻ

b. ተፈታኞች

c. የተፈታኞች ቤተሰቦች፣

d. ፈታኝ መምህራንንና የፈተና አስፈጻሚዎችን

e. የክልል/ከተማ አስተዳደር ት/ት ቢሮዎች አመራርና ባለሙያዎችን፣

f. የክልል የፌዴራል የጸጥታ አካላትን በተለይም የፌዴራል ፖሊስ፤ የክልል ፖሊስና ልዩ ኃይልን አመራርና አባላትን

g. -የዩኒቨርሲቲ አመራርና ማህበረሰብ፣

h. -የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣

i. -የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን፣

j. የሚዲያ አካላት፣

k. የትራንስፖርትና ሎጅስቲክ ሚ/ርና በመዋቅሩ ላይ ያሉ አመራርና ባለሙያዎችን፣

l. የኢንፎርሜሽን መረብ ደህነት አስተዳደር አመራርና ባለሙያዎችን፣

m. ብሔረዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት አመራርና ባለሙያዎችን፣

n. መከላከያ ሚኒስቴር አመራርና ባለሙያዎችን፣

o. የፌዴራልና የክልል የፈተና አስስፈጻሚ ግብረ ኃይል አባላትን

p. አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ተቋም አመራርና ባለሙያዎችን፣

q. በድጋፍና ክትትል እንዲሁም በጀት በመመደብ ያስተባበሩ የመሩ አካላትን ከልብ እናመሰግናለን፡፡

በመጨረሻም የትምህርት ሚኒስቴርና የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት አመራርና ሠራተኞች ያለ እረፍትና ያለ በቂ እንቅልፍ በከፍተኛ መነሳሳትና ቁርጠኝነት ከፈተና ዝግጅት እስከ መፈተን ላደርጉት በጎ አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

## 11. ማጠቃለያ

የ2014 የትምህርት ዘመን የ12ኛ ክፍል ፈተና ከፍተኛ የትምህርት ሚኒስቴር የአመራር ቁርጠኝነት የታያበት እና ውጤታማ የባለድርሻ አካላት ቅንጅት የተስተዋለበት ነው፡፡ ስለሆነም በአጠቃላይ የተሳካ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ከሁሉ በላይ በርካታ ከንቱ ጥረቶች ቢደረጉም ፈተናው አልተሰረቀም፡፡ የአፈታተን ሂደቱም ቢሆን በከፍተኛ አመራሩ በቅርበት የተመራና ከጥቃቅን ጉዳዮች በቀር ያለ መሠረታዊ ችግር ተጠናቋል፡፡ ከሁሉ በላይ የፈተናው ሂደትና የተወሰዱት እርምጃዎች በባለድርሻ አካላትና በአብዛኛው ህብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱ በቀጣይ ያለምንም እንከን ፈተና አዘጋጅቶ በመፈተን የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥና ለማሻሻል የሚደረገውን ጥረት በእጅጉ የሚያግዝ እንዲሆን በማስቻልና አጠቃላይ ሂደቱን የበለጠ የማዘመን ሥራ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

ጠንካራ የምዘና ስርአት ለትምህርት ጥራት!!

////=====///====///